## የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ (አርሺም) ፡ ከአንባቢዎች ፡ ጋር ፡ ለማስተዋወቅ ፡ ስለመጀመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ካቢኔት ፡ አንዳንድ ፡ ሰነዶች፡፡*

### ከሰላሙ ፡ በቀለና ፡ ከዥክ ፡ ቫንደርሊንደን ፡
### የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ለማስተዋወቅ ፡ ያሀል ፡፡

በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የትምህርት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ መዝገብ፡ ቤት ፡ ለማቋቋም ፡ ወሰነ ፡፡

የዚህ ፡ የሕግ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ መቋቋም ፡ በሚከተሉት ፡ ሦስት ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ የተደገፈ ፡ ነው ፡

(፩) ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ውድ ፡ የሆኑትን ፡ ማለት ፡ ድንገት ፡ የጠፉ ፡ ወይም ፡ የተበላሹ ፡ እንደሆነ ፡ መተኪያ ፡ የሌላቸውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሰነዶች ፡ በደህና ፡ ቦታ ፡ መሰብሰብ ፡ መጀመር ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ፡ ተገኘ ፡፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩ ፡ አንዳንድ ፡ የነዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሰነዶች ፡ መጥፋታቸውና ፡ ለመተካትም ፡ ያላቸው ፡ ዕድል ፡ የመነመነ መሆኑ ፡ የተገለጸ ፡ ነው ፡፡

(፪) ሰነዶቹ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተሰበሰቡ ፡ የፈለጋቸው ፡ ሰው ፡ በቀላሉ ፡ እንዲያገኛቸው ፡ በክፍል ፡ በክፍል ፡ መዘጋጀት ፡ አለባቸው ፡፡

(፫) በመጨረሻም ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱን ፡ ሁናቴ ፡ ለማወቅ ፡ የሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ ቢኖሩ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ በሁለቱ ፡ ነገሮች ፡ የተደረገውን ፡ መሻሻል ፡ እንዲያውቁ ፡ ማድረግ ፡ ተፈላጊ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ፡፡

የመጀመሪያው ፡ ሰነዶችን ፡ የመሰብሰብ ፡ ሥራ ፡ የተጀመረው ፡ በግንቦት፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ፡፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ መቀመጥ ፡ አለበት ፡ የሚባለውን ፡ በጃቸው ፡ የነበረውን ፡ ጽሑፍ ፡ ሁሉ ፡ ለመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ እንዲያስረክቡ ፡ የፋኩልቲው ፡ ባልደረቦች ፡ ተጠየቁ ፤ አሁን ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ሰነዶች ፡ አብዛኞዎቹ ፡ ከነሱ ፡ የተገኙ ፡ ናቸው ፡፡ ከተማሪዎችም ፡ አሁን ፡ ለማግኘት ፡ እስቸጋሪና ፡ አብዛኞዎቹ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ አገኘን ፡፡ በመጨረሻም ፡ የፋኩልቲው ፡ ባልደረባ ፡ የሆኑት ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ኃላፊ ፡ ተፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ጽሑፎች ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ ምንጭ ፡ በመልክ ፡ በመልኩ ፡ መፈለግ ፡ ጀመሩ ፡፡

የመጀመሪያው ፡ የ፮ወር ፡ ሥራችን ፡ በግምት ፡ ፻፶ ፡ የሚሆኑ ፡ ሰነዶችን ፡ አስገኝቶልናል ፡፡ ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ የሚከተሉት ፡ ይገኛሉ ፡

---

* ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ የተጻፈው ፡ በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቀ - ኃ - ሥ - ዩኒቨርስቲ ፡ አስተማሪ ፡ በዶክተር ፡ ጂ ፡ ቫንደርሊንደንና ፡ በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቀ - ኃ - ሥ - ተማሪ ፡ አቶ ፡ ሰላሙ ፡ በቀለ ፡ የጋራ ፡ ጥረት ፡ ነው ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ይህን ፡ ጽሑፍ ፡ ስናዘጋጅ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሥራ ፡ ድርሻችን ፡ የተለያየ ፡ ቢሆንም ፡ ሥራውን ፡ የተካፈልነው ፡ እኩል ፡ ነው ፡፡ ጽሑፉ ፡ አሁን ፡ ባለበት ፡ ሁኔታ፡ እያንዳንዳችን ፡ በሙሉ ፡ ኃላፊነት ፡ ለመውሰድ ፡ ዝግጁ ፡ ነን ፡፡

— በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፤

— ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ ዝግጅት ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ሰነዶች ፡ አብዛኛ ምቹ ፡ በረቂቅ ፡ መልክ ፤

— ሲታወጅ ፡ የታተመ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ለማግኘት ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆነ ፡ ሕግ ፤

— ዝክረ ፡ ነገርና ፡ የጉዞ ፡ መግለጫ ፡ የመሰሉትን ፡ ከታሪክ ፡ ምንጮች ፡ የወጡ ፡ ሕግ ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፤

— በሕግ ፡ ፋኩልቱ ፡ ተማሪዎች ፡ የተጻፉ ፡ ጽሑፎች ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ከአማርኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ትርጉሞች ፡ ሲሆኑ ፡ ባንዳንድ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ የተለየ ፡ ጥናት ፡ የተደረገባቸውም ፡ ይገኛሉ ።

— ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግና ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሊቃውንት ፡ የተደረጉ ፡ ጥናቶች ።

የሰነዶቹ ፡ መሰብሰብ ፡ በሚካሄድበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ሰነዶቹ ፡ በየዓይነታቸው ፡ የሚከፋፈሉት ፡ (የሚመደቡት) የሕግ ፡ ፋኩልቴን ፡ የመጽሐፍ ፡ አያያዝ ፡ ዘዴ ፡ በመከተል ፡ ነው ። የተገኙት ፡ በየዓይነታቸው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተመደቡ ፡ በመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ የተወሰነላቸውን ፡ ቦታ ፡ ይይዛሉ ፡ በመጨረሻም ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱን ፡ ሁናቴ ፡ ለመከታተል ፡ የሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ እንዳሉ ፡ እንዲያውቁ ፡ በማለት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ በየጊዜው ፡ የሚገኙትን ፡ ሰነዶች ፡ ዝርዝርና ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ሰነዶች ፡ የተመረጡ ፡ አንባቢዎቹን ፡ የሚማርኩትን ፡ ለማተም ፡ ተስማምቷል ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘረው ፡ የዚህን ፡ አጭር ፡ ጽሑፍ ፡ ርእስ ፡ ይገልጻል ፤ ጽሑፉ ፡ መዝገብ ፡ ቤቱን ፡ ከማስተዋወቅና ፡ የተሰበሰበውን ፡ የሰነዶች ፡ ብዛት ፡ ዝርዝር ፡ ከመስጠቱ ፡ ሌላ ፡ መጽሔቱን ፡ ለሚያነቡ ፡ ሰዎች ፡ በ፲፰፻፹፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአፄ ፡ ምኒሊክ ፡ ስለተቋቋመው ፡ ስለ ፡ መጀመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ካቢኔት ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ሰነዶችን ፡ ያቀርባል ።

የጽሑፎቹ ፡ መታተም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱን ፡ ሁናቴ ፡ የመከታተል ፡ ፍላጎት ፡ ማሳደር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ (መዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ለሁሉም ፡ ጥቅም ፡ ሊሰፋፋ ፡ የሚችለው ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ትንሽ ፡ ቢሆን ፡ በነሱ ፡ እርዳታ ፡ ብቻ ፡ ነው) ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግና ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ እውቀትን ፡ ይጨምራል ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

## <u>ስለ ፡ መጀመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ካቢኔት ፡ አንዳንድ ፡ ሰነዶች።</u>[1]

ምንም ፡ እንኳን ፡ ከዳግማዊ ፡ ሚኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በፊት ፡ የተወሰነ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የነበሩ ፡ ቢሆንም ፡ (ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ የታወቁ ፡ መሆኑን ፡ የምናውቀው ፡ አፈ ፡ ንጉሡን ፡ ነው ፡ )[2] በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ካቢኔ ፡ የተመሠ

1. የዚህ ፡ ክፍለ—ጽሑፍ ፡ ዓላማ ፡ በአባሪዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ሰነዶች ፡ ባጭሩ ፡ ለማስተዋወቅ ፡ ነው ፤ የሰነዶቹን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ክፍለ ፡ ጽሑፉ ፡ አይመለከትም ።

2. ስለዚህ ፡ ነገር ፡ በአባ ፡ ጳውሎስ ፡ ጻድዋ ፡ የተደረገውን ፡ በመዝገብ ፡ ቤት ፡ የሚገኘውን ፡ ምርምር ፡ ይመለከቷል ፡ (ኤስ ፡ ፪) ፤ ይህ ፡ ምርምር ፡ አግባብ ፡ ወደአለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍና ፡ አልቫሬዝ ፤ <u>ፕሬስተር ፡ ጆን ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ኢንዲስ ፡</u> (መዝገብ ፡ ቤት ፡ ኤስ ፡ ፩) ፡ ለሚለው ፡ እትሞቻቸው ፡ ፲ ፡ ደብልዩ ፡ ቢ ፡ ሐንቲንግፎርድ ፡ ወዳዘጋጁቸው ፡ ማስረጃዎች ፡ ሰነዶች ፡ ይመራል ።

ረተው ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒሊክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በ፲፱፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ።[3] እንዲያውም ፡ አባሪ ፡ ፩ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ሰነዶች ፡ በግልጽ ፡ እንደሚያሳዩት ፤ ንጉሡ ፡ ካቢኔ ፡ ለመመስረት ፡ የነበራቸው ፡ አሳብ ፡ በሕዳር ፡ ወይም ፡ በጥቅምት ፡ ፲፰፻፺፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ በአገሩ ፡ ይወራ ፡ ነበር ።[4]

ለ ፡ ሰመር ፡ ደ ፡ ኢቶፒ ፡ የተባለው ፡ በፈረንሣይኛ ፡ ቋንቋ ፡ በሐረር ፡ ይታተም ፡ የነበረው ፡ ጋዜጣ ፡ በሕዳር ፡ ፲፰፻፺፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እትሙ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥቱ፡ ካቢኔ ፡ ለማቋቋም ፡ የነበራቸው ፡ አሳብና ፡ ለጊዜው ፡ በካቢኔው ፡ ውስጥ ፡ ይሰራሉ ፡ የተባሉት ፡ የአራት ፡ ሰዎች ፡ ስምና ፡ ሥራቸው ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ ገለጸ ። ይህ ፡ የመጀመሪያው ፡ ዝርዝር ፡ ከመጨረሻው ፡ ዝርዝር ፡ በሁለት ፡ አቋም ፡ ይለያያል ፡ አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ነሲቡ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሆነው ፡ ተሾሙ ፡ እንጂ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ አልሆኑም ፡ (ያን ፡ ጊዜ ፡ የጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ፈጽሞ ፡ በደንብ ፡ አልተቋቋመም) ፤ እንደዚሁም ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ከተማ ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ እንጂ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሆነው ፡ አልተሾሙም ። በተጨማሪም ፡ ለ ፡ ሰመር ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ይሆኑ ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ የሦስት ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ጠቅሶ ፡ ነበር ። ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ አንዳቸው ፡ ብቻ ፡ የካቢኔ ፡ ሥራ ፡ አገኙ ። ነጋድራስ ፡ ኃይለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የንግድና ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሆነው ፡ ተሾሙ ፡ እንጂ ፡ ለ ፡ ሰመር ፡ እንደተነበየው ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ፡ አልሆኑም ። ደጃዝማች ፡ መሸሻ ፡ ወርቄና ፡ ነጋድራስ ፡ ይገዙ ፡ ግን ፡ አልተሾሙም ።

ለ ፡ ሰመር ፡ በመጋቢት ፡ ፲፱፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እትሙ ፡ ትክክለኛና ፡ የተሟላ ፡ የክቡራን ፡ ሚኒስቴሮቹ ፡ ዝርዝርና ፡ ካቢኔው ፡ የታወጀበት ፡ ቀን ፡ ጥር ፡ እንደሆነ ፡ ይገልጽልናል ። በዚህ ፡ አዋጅ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ የያዙ ፡ ዘጠኝ ፡ ሚኒርቴሮች[5] ፡ ተሾሙ ።

እነርሱም ፡ የሚከተሉት ፡ ነበሩ ።

| | | |
|---|---|---|
| ፩ ፤ | አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ነሲቡ ፡ | የፍርድ ፡ ሚኒስትር |
| ፪ ፤ | ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ | የጦር ፡ ሚኒስትር ። |
| ፫ ፤ | ፀሐፊ ፡ ትዕዛዝ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ | የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ፡ |

3. ስለነዚህ ፡ ታሪካዊ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ባላምበራስ ፡ ማሕተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ ዝክረ ፡ ነገር ፡ (አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፵) ፤ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፪ ፡ የተጠቀሱትን ፡ አባ ፡ ጳውሎስንና ፡ ገብረ፡ሥላሴ፡ክሮኒክ፡ ዱ ሬኝ ፡ ደ ፡ ሚኒሊክ ፡ ደዚያም ፡ ሮይ ፡ ደርዋ ፡ ደ ፡ ኢቶፒ ፡ (፲፱፻፴፪) ፡ ቮል ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፭፻፳፯—፭፻፳ ፡ እና ፡ ለዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፉትን ፡ ማስታዎሻዎች ፡ ይመለከቷል ።

4. በአባሪ ፡ ፩ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ከለሰመር ፡ ደ ፡ ኢቶፒ ፡ ፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ህዳር ፡ ፲፰፻፺፱ ፡ ዓ ፡ ም፡ ገጽ፡፫፻፩ና ፡ ፬ኛ ፡ ዓመት ፡ የኩቲት ፡ ፲፱፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ገጽ ፡ ፫፻፶—፫፻፶፩ ፡ የተወሰደውን ፡ ይመለከቷል ።

5. የተርጓሚ ፡ ማስታወሻ ፡ “ Ministry ” ለሚለው ፡ ቃል ፡ አማርኛው ፡ ሚኒስቴር ፡ ሲሆን ፡ “ Minister ” ለሚለው ፡ ደግሞ ፡ ሚኒስትር ፡ ነው ፡ በሚኒስትሮቹ ፡ ደንቦች ፡ ውስጥ ፡ ሚኒስቴር ፡ እና ፡ ሚኒስትር እንደተመሳሳይ ፡ ወስደው ፡ በማለዋወጥ ፡ ተጠቅመውባቸዋል ። በደንቦቹ ፡ ውስጥ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የተጠቀሙበት ፡ ሚኒስቴር ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ነው ። ሚኒስትር ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ የተጠቀሙበት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ግን ፡ ሚኒስቴር ፡ ከሚለው ፡ ቃል ፡ የተለየ ፡ ትርጉም ፡ ሳይኖረው ፡ ነው ። መምሬ ፡ ብሥራት ፡ በምሳሌ ፡ ጽሑፋቸው ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሙበት ፡ ቃል ፡ ሚኒስቴር ፡ የሚለውን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ግን ፡ እሳቸው ፡ ቃሉን ፡ የተጠቀሙበት ፡ ሰውን ፡ እንጂ ፡ መሥሪያ ፡ ቤትን ፡ ለመጥቀስ ፡ እንዳልነበረ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

፬ ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ከተማ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትር ።
፭ ፡ በጅሮንድ ፡ ሙሉጌታ የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ።
፮ ፡ ነጋድራስ ፡ ኃይለ ፡ ጊዮርጊስ የንግድና ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር
፯ ፡ ከንቲባ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ የእርሻና ፡ የእንዱስትሪ ፡ ሚኒስትር
፰ ፡ አዛዥ ፡ መታፈሪያ ፡ የግቢ ፡ ሚኒስትር ፡
፱ ፡ ቀኛዝማች ፡ መኰንን ፡ ተወንድ ፡ በላይ ፡ የሥራ ፡ ሚኒስትር ።

ካቢኔው ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ የለንም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዳግማዊ ፡ ሚኒሊክ ፡ ለዘጠኙ ፡ ሚኒስቴሮች ፡ የታቀዱት ፡ ደንቦች ፡ እንደ ፡ እድል ፡ ሆኖ ፡ ባላምበራስ ፡ ማሕተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ በጻፉት ፡ በዝክረ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ።[6] ስለእያንዳንዱ ፡ ሚኒስቴር ፡ የወጣው ፡ ደንብ ፡ የሚኒስቴሩን ፡ ሥልጣንና ፡ ግዴታ ፡ በግልጽ ፡ ሥልጣኑ ፡ የት ፡ ድረስ ፡ እንደሆነ ፡ ይለያል ። አንዳንዶቹ ፡ የደንቡ ፡ ጽሑፎች ፡ ረዘም ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፤ አንዱ ፡ (ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የወጣው ፡ ደንብ ፡ ) ፳፮ ፡ አንቀጾች ፡ አሉት ። አንዳንዶቹም ፡ በጣም ፡ አጠር ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። (ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የወጣው ፡ ደንብ ፡ አራት ፡ አንቀጾች ፡ ብቻ ፡ የያዘ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የእፈንጉሥ ፡ ሥራ ፡ ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ የታወቀ ፡ ስለሆነ ፡ ከአራት ፡ አንቀጾች ፡ በላይ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስላልተገኘ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።) ከአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ በስተቀር ፡ ሁሉም ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ቤተ ጨማሪ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚገባቸው ፡ መግለጫ ፡ ይሰጣቸው ፡ ነበር ። የሕዝብ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ የሚተዳደረው ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለነበረ ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴርም ፡ ስለ ፡ ሕዝብና ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ መግለጫ ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ። የንግድና ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴርም ፡ በኃላፊነቱ ፡ ሥር ፡ ስለሚገኙት ፡ ስለንግድና ፡ ስለ ፡ ውጭ ፡ ጉዳይ ፡ መግለጫ ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ።

እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ በዝክረ ፡ ነገር ፡ እንዳሉ ፡ ሆነው ፡ በሚከተሉት ፡ ገጾች ፡ እንዲታተሙ ፡ አድርገናል ። (አባሪ፪)

ዳግማዊ ፡ ምኒሊክ ፡ ሚኒስቴሮቹን ፡ እንዳቋቋሙ ፡ ትንሽ ፡ ጊዜ ፡ ቆይተው ፡ መምሬ ፡ ብስራት ፡ የተባሉ ፡ መንዜ ፡ ስለ ፡ አዲሶቹ ፡ ሚኒስቴሮች ፡ በምሳሌ ፡ መልክ ፡ የሚገልጽና ፡ የሚያስተምር ፡ ትንሽ ፡ ጽሑፍ ፡ አሳትመው ፡ ነበር ። ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በአገሩ ፡ ከታተሙት ፡ መጽሐፎች ፡ ሁለተኛው ፡ ለመሆኑ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡[7] ሕግ ፡ ነክ ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ ስለሆነ ፡ ልናውቀው ፡ ያሻናል ። ጽሑፉ ፡ በሙሉ ፡ በአባሪ ፡ ፫ ፡ ይገኛል ።

የምሳሌው ፡ ጽሑፍ ፡ አዲስ ፡ የተመሠረተውን ፡ ካቢኔ ፡ ከሰው ፡ አካላት ፡ ጋር ፡ የሚያወዳድርና ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጽሑፎች ፡ የተወሰደ ነው ።[8] የጽሑፉ ፡ ጠቅላላ ፡ አሳማ ፡ አዲሶቹ ፡ ድርጅቶች ፡ የንጉሡ ፡ ነገሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ የሚከፋፍሉና ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒሊክን ፡ ሥልጣን ፡ የሚያደክሙ ፡ ናቸው ፡ የሚሉትን ፡ ሰዎች ፡ በመቃረን ፡ በንጉሡ ፡ ነገሥቱና ፡ በአዲሶቹ ፡ ሚኒስ

---

6. እላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፩ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰ ። እነዚህን ፡ ሰነዶች ፡ ለመተርጐምና ፡ ለማሳተም ፡ ለፈቀዱልን ፡ ለክቡር ፡ ባላምበራስ ፡ ማሕተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ምስጋናችንን ፡ እንገልጻለን ።
7. ኤስ ፡ ራይት ፡ "የመጻሕፍትና ፡ የብራና ፡ ጽሑፎች ፡ ስብሰባ ፡ በኢትዮጵያ" የኢትዮጵያ ፡ ጥናት መጽሔት ፡ ፫ል ፡ ፪ ፡ ፩ ፡ (ጥር ፲፱፻፶፮) ፡ በተለይ ፡ ገጽ ፡ ፲፫—፲፱ ፡ ይመለከቷል ።
8. ለአንባቢው ፡ እንዲመች ፡ በማለት ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ጽሑፎች ፡ ከአባሪ ፫ ፡ ጋር ፡ ከሚሄዱት ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻዎች ፡ ውስጥ ፡ ጨምረናቸዋል ።

ቴሮች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ አንድነት ፡ ለማሳየት ፡ ነበር ። የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጥቅሶች ፡ ለጽሑፉ ፡ ያላቸው ፡ አስፈላጊነት ፡ በጣም ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ (አንዳንድ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ጸሐፊው ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ሳይለውጡ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጽሑፎቹን ፡ አትመዋቸዋል ።) ነገር ፡ ግን ፡ የሚነጻጸረው ፡ ነገር ፡ የት ፡ እንዳለ ፡ አንዳንዴ ፡ ለማየት ፡ አይቻልም ። ሆኖም ፡ ጽሑፉን ፡ ለመመርመር ፡ የተነሳንበት ፡ ጉዳይ ፡ አይደለም ። የኛ ፡ አላማ ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ሚኒስቴር ፡ ለተረቀቁት ፡ ደንቦች ፡ እንዳደረግነው ፡ ሁሉ ፡ ጽሑፉን ፡ ከአንባቢዎቻችን ፡ ጋር ፡ ለማስተዋወቅ ፡ ነው ። እነዚህን ፡ ጥቂት ፡ ጽሑፎች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ወደፊት ፡ አንድ ፡ ሊቅ ፡ ስለመጀመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ካቢኔ ፡ ሙሉ ፡ ታሪክ ፡ በሰፊው ፡ ያትታል ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

## አባሪ ፡ ፩

<u>ስለ ፡ መጀመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ካቢኔ ፡ መሾም ፡ ለ ፡ ሰመር ፡ ደ ፡ ኢቶፒ ፡ በተባለው ፡ ጋዜጣ ፡ የቀረቡ ፡ ጽሑፎች ፡ (ለ ፡ ሰመር ፡ ደ ፡ ኢቶፒ ፤ ፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ህዳር ፡ ፲፱፻ ፤ ገጽ ፡ ፫፻፩ ፡ እና ፡ ፬ኛ ፡ ዓመት ፤ የካቲት ፤ ፲፱፻፩ ፤ ገጽ ፡ ፫፻፶፬ — ፫፻፶፭)</u>[1]

### <u>፩ ፤ ህዳር ፤ ፲፱፻ ፡ የሚኒስቴር ፡ መቋቋም ።</u>

በጥቅምት ፡ ወር ፤ እንደ ፡ ኤውሮፓውያን ፡ ዓይነት ፡ ሚኒስቴር ፡ በማቋቋም አፄ ፡ ሚኒሊክ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተደርጐ ፡ የማያውቅ ፡ መሻሻል ፡ አደረጉ ።

ለማወቅ ፡ ያህል ፡ ለሚኒስቴርነት ፡ እጩ ፡ ነበሩ ፡ ተብለው ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ የሚታወቁት ፡ የሚቀጥሉት ፡ ናቸው ፤

| | |
|---|---|
| የጉባዔው ፡ ፕሬዚዳንት | አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ነሲቡ[2] |
| የጦር ፡ ሚኒስትር | ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ |
| የፍርድ ፡ ሚኒስትር | ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ከተማ ፡ |
| የእርሻ ፡ ሚኒስትር | ከንቲባ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ። |

የሚከተሉትም ፡ ለሚኒስትርነት ፡ እጩ ፡ ናቸው ፡ ይባል ፡ ነበር ፡ ደጃዝማች ፡ መሸሻ ፡ ወርቄ ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ። ነጋድራስ ፡ ይገዙ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ። ነጋድራስ ፡ ኃይሉ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ።

### <u>፪ - የካቲት ፡ ፲፱፻፩ ፡ ስለ ፡ አዲሶቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሚኒስትሮች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ።</u>

ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባወጣነው ፡ እትም ፡ የመጀመሪያውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሚኒስቴር ፡ መቋቋም ፡ አስታውቀን ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ የተረጋገጠ ፡ መግለጫ ፡ ስላገኘን ፡ የተሾሙትን ፡ ሚኒስትሮች ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ ልናሻሽለውና ፡ ልናሟላው ፡ ችለናል ።

---

1. የሚቀጥሉት ፡ ጽሑፎች ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ የተተረጐሙት ፡ መጀመሪያ ፡ ከተጻፈበት ፡ ከፈረንሣይኛው ፡ ከተተረጐመው ፡ የእንግሊዘኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ።
2.

ከዚህ ፡ በፊት ፡ የተሾሙት ፡ ሰባቱ ፡[3] እና ፡ ሌሎች ፡ ሁለት ፡ ሹመታቸው ፡ ግቢ ፡ እሁድ ፡ ጥር ፡ ፲፰ ፡ በይፋ ፡ ተገለጸ ።

<u>የድሮ ።</u>

| | |
|---|---|
| የፍርድ ፡ | አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ነሲቡ ። |
| የውጭ ፡ ጉዳይና ፡ የንግድ | ነጋድራስ ፡ ኃይሌ ፡ ጊዮርጊስ ። |
| የገንዘብ ፡ | በጅሮንድ ፡ ሙሉጌታ ። |
| የእርሻ ፡ | ከንቲባ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ። |
| የጦር ፡ | ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ |
| የጽሕፈት ፡ | አለቃ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ |

<u>አዲስ ።</u>

| | |
|---|---|
| የሥራ ፡ | ቀኛዝማች ፡ መኰንን ። |
| የግቢ ፡ | አሳላፊ ፡ መታፈሪያ ። |

## አባሪ ፡ ፪

<u>ስለሚኒስቴሮች ፡ አቋቋም ፡ ምኒሊክ ፡ ያወጧቸው ፡ ድንጋጌዎች ።</u>

<u>ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ደንብ ። (ዝክረ ፡ ነገር</u> ፡ ገጽ ፡ ፻፱—፻፲)

፩ኛ ፤ ይህ ፡ ሚኒስቴር ፡ የንጉሥ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሆኖ ፡ ምስለኔ ፡ ሆኖ ፡ የሾ ሞን ፡ ግዛት ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቃል ፤ ርሱ ፡ ነው ፡ የንጉሡም ፡ ምስለኔ ፡ በገዢዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ።

፪ኛ ፤ የንጉሡን ፡ ትእዛዝ ፡ ወደ ፡ ገዢዎቹ ፡ ለመላክ ፡ የሱ ፡ ሥራ ፡ ነው ፤ በየከተማው ፡ መንግሥት ፡ ሹም ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እኒህ ፡ ሹሞች ፡ ለዚህ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይታዘዛሉ ።

፫ኛ ፤ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የዱል ፡ ጭፍራ ፡ አለቃ ፡ ነው ፤ ያገር ፡ ግ ዛት ፡ ሁሉ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ለሱ ፡ ይታዘዛሉ ። እሱም ፡ የሰው ፡ ሕይወት ፡ ዋና ፡ ጠባቂ ፡ ነውና ፤ ያገር ፡ ነዋሪዎችን ፡ ሁሉ ፡ ዐማራን ፡ ፈረንጅን ፡ ጋላን ፡ ሌሎች ንም ፡ ይጠብቃል ።

፬ኛ ፤ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴርን ፡ ያስታውቃሉ ። ባገራቸው ፡ በጤና ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እሱ ፡ ከጤና ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋራ ፡ ተስማምተው ፡ የሰው ፡ ጤና ፡ ይጠ ብቃሉ ፤ የሚያስፈልግ ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ።

፭ኛ ፤ ይህ ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ በያገሩ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያስቈጥራል ፤ አገረ ፡ ገዢዎችንም ፡ እያዘዘ ፡ በየግዛታቸው ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ የሚያስቆጥር ፡ እሱ ፡ ነው ።

፮ኛ ፤ ካገረ ፡ ገዢዎች ፡ ዘንድ ፡ የሚመጣውን ፡ የሰውን ፡ ቊጥር ፡ ባመት ፡ ባመቱ ፡ በትልቅ ፡ መዝገብ ፡ ያስገለብጣል ።

---

3. ሳ ፡ ሰመር ፡ ደ ፡ ኢቶፒ ፡ መኳስ ፡ ከተማ ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትርን ፡ በመርሳት ፡ የሚጠቅሳቸው ፡ ስድስት ፡ ሚኒስትሮችን ፡ ብቻ ፡ ሲሆንም ።

፫ኛ ፤ ይህም ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የተወለዱበትንና ፡ የሞቱበትን ፤ ሚስት ፡ ያገቡትን ፡ ሰዎች ፡ እንደዚሁ ፡ በመዝገብ ፡ ያጽፋል ፡፡

፬ኛ ፤ ባመት ፡ ባመት ፡ አገሬ ፡ ገዢዎች ፡ የሚልኩትን ፡ የመዝገብ ፡ ግልባጭ ፡ ለንጉሡና ፡ ለቀሩት ፡ ሚኒስቴሮች ፡ አሳይቶ ፡ በትልቅ ፡ መዝገብ ፡ አስገልብጦ ፡ በመንግሥት ፡ ሣጥን ፡ ይቀመጣል ፡፡

፭ኛ ፤ በሰውነቱና ፡ በቤቱ ፡ ግብር ፡ የሚያቆም ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ የመኳንንትን ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ የሰው ፡ ቍጥር ፡ አስቦ ፡ እንደ ፡ ተላከበት ፡ ሒሳቡንም ፡ ጨምሮ ፡ የመዝገቡንም ፡ ግልባጭ ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይሰጣል ፡፡

፮ኛ ፤ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥራው ፡ ባ፫ ፡ ይከፈላል ፡፡

፩ኛ ፤ የሸዋ ፡ ግዛት ፡፡

፪ኛ ፤ የሰሜን ፡ እስከ ፡ ሸዋ ፡ ምሥራቅ ፡ አገር ፡ ከጐዣም ፡ ዠምሮው ፡ እስከ ፡ አዳል ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ በትግሬና ፡ በወሎ ፡ አገር ፡ በኩል ፡፡

፫ኛ ፤ የሸዋ ፡ ደቡብና ፡ ምዕራብ ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ ከሐረር ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ጐዣም ፡ ድረስ ፡ በከፋና ፡ በጅማ ፡ አገር ፡ በኩል ፡፡

፬ኛ ፤ የሰው ፡ ቍጥርና ፡ ጽፈት ፡፡

፭ኛ ፤ የከተማ ፡ ዘበኛ ፡ የዱል ፡ ጭፍራ ፡፡

<u>የውጭ ፡ አገር ፡ ሚኒስቴር ፡ ደንብ ፡ (ዝክረ ፡ ነገር</u> ፡ ገጽ ፡ ፫፻፹፫—፫፻፺፩)

መዠመሪያ ፡፡

የዚህ ፡ ሚኒስቴር ፡ ዋና ፡ ሥራ ፡ የእንግዶች ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ከሌላ ፡ መንግሥት ፡ ከሚኒስትሮቻቸው ፡ ጋራ ፡ ይነጋገራል ፡፡

ሁለተኛ ፡፡

ከሌሎች ፡ መንግሥቶች ፡ ጋራ ፡ ዋና ፡ ፖለቲካ ፡ ነገር ፡ ሲነሣ ፡ ንጉሡ ፡ ራሳቸው ፡ ናቸው ፡ ነገሩን ፡ የሚጨርሱት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አስቀድሞ ፡ ነገሩን ፡ አስተውሎ ፡ መርምሮ ፡ ለንጉሡ ፡ ነገሩን ፡ የሚገልጽላቸው ፡ ሚኒስትሩ ፡ ነው ፡፡

ደግሞ ፡ ንጉሡ ፡ ከመልክተኞቹ ፡ ጋራ ፡ በተነጋገሩ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩ ፡ ከተጨረሰ ፡ በኋላ ፡ የንጉሥ ፡ ወረቀት ፡ አጽፎ ፡ አሳትሞ ፡ የሚሰጥ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ነው ፡፡

ሦስተኛ ፡፡

የውጭ ፡ መንግሥት ፡ መልክተኞች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ትልቅ ፡ እንግዶች ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ ሲመጡ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ የሚያቀርባቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፡፡

አራተኛ ፡፡

መልክተኞችም ፡ የመንግሥታቸውን ፡ ደብዳቤ ፡ ለሱ ፡ ነው ፡ የሚያቀርቡለት ፡፡

አምስተኛ ፡፡

የውጭ ፡ አገር ፡ ሚኒስትር ፡ የቆንስሉና ፡ የሚኒስትሮቻቸው ፡ ዋና ፡ ጠባቂ ፡ ነው ፡፡ ቆንስሎቻቸውና ፡ ሚኒስትሮቻቸው ፡ ክብር ፡ ይገባቸዋል ፤ ከመንግሥቱ ፡ ዘንድ ፡ የተላከ ፡ ሰው ፡ እንዳይነካ ፡ እንዳይመታ ፡ ሐሳብ ፡ እንዳይገባና ፡ እንዳይታሰር ፡ ርሱም ፡ ሚስቱም ፡ ዘመዶቹም ፡ ጸሐፊዎቹም ፡ አቤታቸው ፡ ያሉት ፡

ሰዎች ፣ ሁሉ ፤ የጦርነት ፣ ምክንያት ፣ ይሆናልና ። ደግሞ ፡ ወደ ፣ መልክተኞች፣ ቤት ፣ በግድና ፡ በቍጣ ፡ መግባት ፣ አይሆንም ፤ በዚህ ፣ ምክንያት ፡ ጠብ ፡ ይነሣልና ። ይህነን ፣ ሕግ ፣ ሥርዐት ፣ ባለበት ፣ አገር ፣ ሁሉ ፡ መንግሥት፣ይጠብቃል።

ስድስተኛ ።

ከመንግሥቶች ፡ ጋራ ፣ ስለ ፣ ፖስታ ፣ ስለ ፣ ቴሌግራም ፣ ስለ ፣ ቴሌፎን ፣ ውል ለማድረግ ፣ የሱ ፣ ሥራ ፡ ነው ።

ሰባተኛ ።

ደግሞ ፣ ከሌላ ፣ መንግሥቶች ፡ ጋራ ፡ ውል ፣ የሚያደርግ ፣ በጦርም ፡ ጊዜ ፡ ስለሚያደረግ ፣ የበሽተኞችና ፣ የቁስለኛ ፣ በሚዋጉ ፣ ቦታ ፡ ሰዎች ፡ እንዳይነኩት።

ስምንተኛ ።

ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ አገር ፣ የሚገባ ፣ እንግዳ ፣ ለውጭ ፣ አገር ፡ ሚኒስትር ፡ ወይም ፣ ለምስሌኔዎቹ ፣ ፓስፖር ፣ ደብዳቤ ፡ ያሳያል ።

ዘጠነኛ ።

ለእንግዶች ፣ የሚሰጠውን ፣ የንግድ ፣ ውል ፡ ወይም ፣ የርሻ ፡ ወይም ፣ የሚሥራ ፣ ቤት ፣ ውል ፣ ርሱ ፡ በፊት ፣ ያያልና ፤ በመዝገቡም ፣ ግልባጩን ፣ ይጽፋል ፣ ውል ፡ ከታተመ ፣ በኋላ ።

ዐሥረኛ ።

ከሌላ ፣ አገር ፡ መንግሥት ፡ ርስት ፤ ከእንግዳ ፣ ሰው ፡ ብድር ፣ ለመቀበል ፡ ስለ ፣ ኢትዮጵያ ፣ መንግሥት ፣ ይህ ፣ ሥራ ፡ በሱ ፣ እጅ ፣ ይሆናል ።

ዐሥራ ፣ አንደኛ ።

እንግዳ ፡ በቆንስሉ ፣ ላይ ፣ የኢትዮጵያ ፣ መንግሥት ፣ ሰው ፣ የከሰሰ ፣ እንደ ሆነ ፣ ወደ ፣ ውጭ ፣ አገር ፣ ሚኒስቴር ፣ ነው ፣ የመንግሥት ፡ ጠባቂ ፣ የሚሆን ፡ በዳኝነት ፣ ጊዜ ።

ዐሥራ ፣ ሁለተኛ ።

ስለ ፣ ፖለቲካ ፡ ወይም ፣ ስለ ፡ ሌላ ፣ ነገር ፣ ከኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ እንግዳ ፣ ለማስወጣት ፣ መንግሥት ፡ የፈለገ ፣ እንደ ፡ ሆነ ፣ የውጭ ፣ አገር ፡ ሚኒስትር ፡ ነው ፣ ከዚህ ፡ እንግዳ ፣ ቆንስል ፣ ጋር ፣ ተነጋግሮ ፣ ነገሩን ፣ የሚጨርስ ።

ዐሥራ ፡ ሦስተኛ ።

ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥትና ፣ ከዳር ፡ አገር ፣ ሚኒስቴሮች ፡ ጋራ ፡ ውል ፡ አለ ፣ በደለኛ ፣ ስለ ፣ ማስወጣት ፣ ወይም ፣ ስለ ፡ ማስገባት ፤ ይህ ፣ ሥራ ፣ የውጭ፣ አገር ፣ ሚኒስቴር ፡ ሥራ ፣ ነው ፤ ከበደለኛ ፣ ቆንስል ፡ ጋራ ፡ ተስማምቶ ።

ዐሥራ ፡ አራተኛ ።

ስለ ፡ ፓስፖር ፣ ደብዳቤና ፡ ስለ ፡ በደለኛ ፣ ማስወጣት ፡ ለሚኒስቴሩ ፣ የዳር አገር ፣ ሁሉ ፣ ገዢዎች ፡ የርሱ ፣ ምስለኔ ፣ ይሆናሉ ።

ዐሥራ ፣ አምስተኛ ።

የውጭ ፡ አገር ፣ ሚኒስትር ፡ የኢትዮጵያ ፣ ቆንስሎችና ፡ መልክተኞች ፣ ሁሉ ፣ አለቃ ፣ ነው ፤ አዲስ ፣ ቆንስል ፣ ስለ ፣ ማድረግ ፣ ያስፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

ርሱ ፡ ነው ፡ ለንጉሥ ፡ የሚያመለክታቸው ፤ ቆንስሎቹም ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ይነጋገራሉ ፡ ስለ ፡ ሥራቸው ።

## ዐሥራ ፡ ስድስተኛ ።

ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ መልክተኞች ፡ ለመላክ ፡ የንጉሥ ፡ መልክት ፡ ነው ፤ መንግሥት ፡ በሌላ ፡ መንግሥት ፡ ፊት ፡ የታወቀ ፡ እንዲ ፡ ሆኖ ፡ መልክተኞች ፡ ይላካል ፤ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በኤሮፓ ፡ አገር ፡ ሚኒስትሮች ፡ እስቲያደርግ ፡ ድረስ ፡ ፈረንጆችን ፡ እዚያ ፡ ቆንስል ፡ መሾም ፡ ይችላል ፤ ደመወዝ ፡ ሳይሰጣቸው ፡ ከወረቀትና ፡ ከፖስታ ፡ ዋጋ ፡ በቀር ። እነኛ ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ አሳቸውና ፡ ስለ ፡ ከበሬታ ፡ ብቻ ፡ ቆንስል ፡ ተብለው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አለደመወዝ ፡ ያገለግላሉ ።

## ዐሥራ ፡ ሰባተኛ ።

የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጅቡቲ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ቆንስል ፡ አለው ። ሌሎች ፡ ቆንስሎች ፡ በኢየሩሳሌም ፤ በዐደን ፤ በምጥዋ ፤ በካርቱምና ፡ በእንግሊዝ ፡ ሱዳን ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ዳርቻ ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

## ዐሥራ ፡ ስምንተኛ ።

የውጭ ፡ አገር ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥራውን ፡ ባራት ፡ ክፍል ፡ ይከፍላል ።

፩ኛ ፤ የቆንስልና ፡ ወደ ፡ ዳር ፡ አገር ፡ ካሉት ፡ መንግሥቶች ፡ ጋራ ፡ መነጋገር ።

፪ኛ ፤ ከሌሎች ፡ መንግሥቶችና ፡ ከሚኒስትሮቻቸው ፡ ጋራ ፡ መነጋገር ።

፫ኛ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ላሉት ፡ እንግዶች ፡ ነገር ፡ ውል ፡ ፓስፖር, ፡ (ደብዳቤ) ።

፬ኛ ፤ መጽሐፍ ፡ ወረቀት ፡ ጋዜጣ ፡ ማስተርጐም ።

<u>የንጉሥ ፡ ግቢ ፡ የፖስታ ፡ የቴሌግራፍና ፡ የቴሌፎን ፡ ሚኒስቴር ፡ ደንብ ፡ (ዝክረ ፡ ነገር</u> ፡ ገጽ ፡ ፬፻፺)

## መጀመሪያ ።

የዚህ ፡ ሚኒስቴር ፡ ዋና ፡ የመንግሥት ፡ ግቢ ፡ መጠበቅ ፡ ነው ።

## ሁለተኛ ።

ባሉበት ፡ ስፍራ ፡ እግቢም ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ ሌላም ፡ ቢሆን ፡ ርሱ ፡ ነው ፡ የርሳቸው ፡ ዋና ፡ ጠባቂ ።

## ሦስተኛ ።

የንጉሥ ፡ ቤት ፡ በየማዕርጉ ፡ አካሄድ ፡ መሪ ፡ ርሱ ፡ ነው ፤ የመንግሥቶች፡ መልክተኛ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ ሲመጣ ፡ ርሱ ፡ ነው ፡ እከተማ ፡ በር ፡ ላይ የሚቀበለው ፤ እስከ ፡ ንጉሡ ፡ ግቢ ፡ ድረስ ፡ ይከተለዋል ፤ ንጉሡ ፡ እስኪቀበሉት ፡ ድረስ ።

## አራተኛ ።

የፖስታ ፡ የቴሌግራፍና ፡ የቴሌፎን ፡ ዋና ፡ አለቃ ፡ ርሱ ፡ ነው ፤ የዚህን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ለሱ ፡ ይታዘዛሉ ፤ በ፲ ፡ በ፲ ፡ ወር ፡ የሥራቸውን ፡ ገቢና ፡ ወጪ ፡ መዝገብ ፡ ያሰናዱለታል ፤ ርሱም ፡ ይህነን ፡ ደብተር ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይሰጣል ።

## የንግድና ፡ የጉምሩክ ፡ ሚኒስቴር ። (ዝክረ ፡ ነገር ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷፯—፫፻፷፰)

### መዠመሪያ ።

ያገር ፡ ንግድ ፡ መጠበቅ ፡ የዚህ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥራ ፡ ነው ።

### ሁለተኛ ።

የኢትዮጵያ ፡ ጉምሩክና ፡ ነጋድራሶች ፡ ሁሉ ፡ አሲቃ ፡ ነው ።

### ሦስተኛ ።

ያገር ፡ ንግድ ፡ የሚያበዛውን ፡ ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ እያስተዋለ ፡ ለመንግሥት ፡ የሚያመለክት ፡ ርሱ ፡ ነው ።

### አራተኛ ።

የጉምሩክ ፡ ሥርዓት ፡ ለነጋዴዎች ፡ የሚመችና ፡ ቀረጥ ፡ የሚያበዛ ፡ አስተውሎ ፡ ለመንግሥት ፡ ያመለክታል ።

### አምስተኛ ።

አዲስ ፡ ቀረጥ ፡ ለማድረግ ፡ ያለውን ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፡ ያስፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ርሱ ፡ ነው ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ በፊት ፡ አስተውሎ ፡ ለመንግሥት ፡ የሚያመለክት ፡ ገቢ ፡ እንዲያበዛ ።

### ስድስተኛ ።

የጉምሩክ ፡ ሒሳብ ፡ በልክ ፡ ሆኖ ፡ በሁለት ፡ መዝገብ ፡ እንዲጻፍ ፡ ይተጋል ።

### ሰባተኛ ።

የሚገባውንና ፡ የሚወጣውን ፡ ዕቃ ፡ በያይነቱ ፡ ለብቻ ፡ ያጽፋል ፤ ባመት፡ መጨረሻ ፡ ለመንግሥት ፡ ድምሩን ፡ እንዲያሳይ ።

### ስምንተኛ ።

በ፫ ፡ በ፫ ፡ ወር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ያገር ፡ ነጋድራሶቹ ፡ የጉምሩካቸውን ፡ ገቢና ፡ ወጪ ፡ ለሱ ፡ ያስታውቃሉ ።

### ዘጠነኛ ።

ባመት ፡ ባመት ፡ ከነጋድራሶቹ ፡ የመጣውን ፡ ደብተር ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ድምሩን ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያሳልፋል ።

### ዐሥረኛ ።

የነጋዴዎች ፡ ዳኛ ፡ ይሆናል ። ስለ ፡ ዳኝነት ፡ አንድ ፡ የሚረዳው ፡ ምስለኔ ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ፤ ስለ ፡ ፈረንጆች ፡ ነገር ፡ ከፈረንጅ ፡ ነጋዴ ፡ አያሌ ፡ መርጦ ፡ መርጦ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ አስተውሎ ፡ ይጨርሳል ።

### ዐሥራ ፡ አንደኛ ።

ቆንስሎች ፡ ዜጋቸውን ፡ ለማገድ ፡ ወደ ፡ ዳኝነት ፡ የመጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የንግድ ፡ ሚኒስትር ፡ ራሱ ፡ መጥቶ ፡ ይፈርዳል ፤ ተጠንቅቆ ፡ መልካም ፡ ሕግ ፡ እንዲጠበቅ ፡ የመንግሥት ፡ ስም ፡ እንዳይጠፋ ።

## ዐሥራ ፡ ሁለተኛ ።

የንግድ ፡ ሚኒስትር ፡ የፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ተሟጋቾቹ ፡ ተመልሶ ፡ ለአፈ ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ ለንጉሥ ፡ ማመልከት ፡ ይችላሉ ።

## ዐሥራ ፡ ሦስተኛ ።

ከሌላ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ የንግድ ፡ ውል ፡ ሲደረግ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የንግድና ፡ የውጭ ፡ ነገር ፡ ሚኒስትሮች ፡ ነገሩን ፡ አስቀድመው ፡ እያስተዋሉ ፡ ለመንግሥት ፡ ያመለክታሉ ፣

## ዐሥራ ፡ አራተኛ ።

በኢትዮጵያና ፡ በሌላ ፡ መንግሥት ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ ሁሉ ፡ ባለወሰን ፡ ነውና ፡ የውሉ ፡ ጊዜ ፡ ሳያልቅ ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ አስቀድመው ፡ የንግድና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሚኒስትሮች ፡ ለመንግሥት ፡ ያስታውቃሉ ።

## ዐሥራ ፡ አምስተኛ ።

ከነጋዴ ፡ መንግሥት ፡ የሚቀበለውን ፡ የንግድና ፡ ያረቂ ፡ ግብር ፡ ርሱ ፡ ነው ፡ የሚያቆመው ፤ ይህንን ፡ ግብር ፡ በወር ፡ በወር ፡ ተቀብሎ ፡ ለመንግሥት ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ይሰጣል ።

## ዐሥራ ፡ ስድስተኛ ።

ባመት ፡ መጨረሻ ፡ ግብር ፡ የተቀበለውን ፡ መዝገብ ፡ ደምሮ ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይሰጣል ።

## ዐሥራ ፡ ሰባተኛ ።

የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የጤና ፡ ሚኒስቴርን ፡ ይረዳል ፤ ያረቂና ፡ የመብል ፡ ሺያጮችን ፡ ሲያስጠብቅ ፡ ዕቃቸው ፡ ለሰው ፡ ጤና ፡ ክፉ ፡ እንዳይሆን ።

## ዐሥራ ፡ ስምንተኛ ።

የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥራውን ፡ ባ፭ ፡ ክፍል ፡ ይከፍላል ።

ሀ) የንግድ ፡ ነገር ፡ ክፍል ።

ለ) ያዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ጉምሩክ ፡ ክፍል ።

ሐ) የቀሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ ጉምሩኮች ፡ ክፍል ።

መ) የሒሳብ ፡ ክፍል ።

ሠ) በንግድ ፡ ነገር ፡ የሚነሣ ፡ ክርክር ፡ ዳኝነት ፡ ክፍል ።

<u>የርሻና ፡ የመሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሚኒስቴር ፡ ደንብ ፡ (ዝክረ ፡ ነገር ፡</u> ገጽ ፡ ፫፻፲፯—፫፻፲፱)

## መዠመሪያ ።

የዚሀ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥራ ፡ የመሥሪያ ፡ ቤትና ፡ ከብት ፡ ማርባት ፡ ነው ።

## ሁለተኛ ።

ምድር ፡ በደኅና ፡ እንዲታረስና ፡ ብዙ ፡ እኽል ፡ እንዲመጣ ፡ የሱ ፡ ሥራ ፡ ነው ፤ የርሻ ፡ መሣሪያ ፡ በደኅና ፡ እንዲሰወጥ ፡ ያዛል ፤ ያለውን ፡ ዓይነት ፡ ቡቃያ፡

ያሳምራል ፤ ሌላም ፡ ዐይነት ፡ ያስጨምራል ፤ አገር ፡ ሀብታም ፡ እንዲሆን ፡ ክብ ትም ፡ ያስረባል ፤ እንደ ፡ ኤሮፓ ፡ አገር ፡ ሥርዓት ።

ሦስተኛ ።

የባላገር ፡ ጥግ ፡ ይሆናልና ፡ ሕጋቸውን ፡ ይጠብቃል ።

አራተኛ ።

በመልካም ፡ መሬታቸውን ፡ ያረሱትን ፡ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ እኽል ፡ ያመጡ ትም ፡ ብዙ ፡ ከብት ፡ ያረቡትን ፡ በደኅና ፡ ገበሬዎች ፡ ያሠሩት ፡ ሹሞች ፡ ክብ ርን ፡ ገንዘብ ፡ ይሰጣል ።

አምስተኛ ።

በደኅና ፡ አገራቸውን ፡ ያላሠሩትን ፡ ሰዎች ፡ አገራቸውንም ፡ ያላሳመሩ ትን ፡ ያስቀጣል ።

ስድስተኛ ።

አንዳንድ ፡ አገር ፡ ክፉ ፡ መከራ ፡ የሆነበት ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ በሽታ ፡ በሰው ፡ ወይም ፡ በከብት ፡ የመጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ለመንግሥት ፡ አማ ላጅ ፡ ይሆናል ። ዐሥራትና ፡ ግብር ፡ እንዲምሩት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ መልካም ፡ መከ ር ፡ ሳገኝ ፡ አገር ፡ ግብሩን ፡ ጥቂት ፡ መጨመር ፡ ያስፈልጋል ፤ በደኸየው ፡ አገር ፈንታ ።

ሰባተኛ ።

የርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ክፉ ፡ መከር ፡ መከልከል ፡ የርሱ ፡ ሥራ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ባላገሮችም ፡ በመልካም ፡ መሬታቸውን ፡ እንዲያርሱ ፡ ይጠባበቃቸዋል ፤ ለሐኪ ሞችም ፡ እንዲታዘዙ ፡ ስለ ፡ ርሳቸውና ፡ ስለ ፡ ከብቶቻቸው ፡ ጤና ።

ስምንተኛ ።

የርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ የመኳንንት ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ ስንት ፡ እርሻ ፡ ስንት ፡ ደን፡ ስንት ፡ ሣር ፡ ስንት ፡ ያልታረሰ ፡ መሬት ፡ እንዳለ ፡ የለማውንም ፡ የተበላሸው ንም ፡ ያያል ።

ዘጠነኛ ።

ከመኳንንት ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ ሁሉ ፡ የመጣውን ፡ ማስታወቂያ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ይጽፋል ።

ዐሥረኛ ።

ዳግም ፡ ያገር ፡ ከብት ፡ ያስቆጥራል ፤ ገዢዎችም ፡ ባመት ፡ ባመት ፡ ያገራ ቸውን ፡ ከብት ፡ ብዛትና ፡ ማነስ ፡ ያስታውቁታል ።

ዐሥራ ፡ አንደኛ ።

ለንግድ ፡ በኪራይ ፡ መሬት ፡ ሲሸጥ ፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሲከፈት ፡ ውል ፡ አድርጎ ፡ የሚያትም ፡ የርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከውጭ ፡ ሚኒስቴር ፡ ከገንዘብ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋራ ፡ ይመካከራሉ ፤ የተፈረመውንም ፡ ውል ፡ ግልባጭ ፡ ከታተመ ፡ በኋላ ፡ ለነዚህ ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ይሰጣል ።

### ዐሥራ ፡ ሁለተኛ ።

በባላገር ፡ የርሻ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተከፈተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነው ፡ የሚጠብቀው ።

### ዐሥራ ፡ ሦስተኛ ።

ከመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋራ ፡ ባገር ፡ የሚሆነውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ስለ ፡ እርሻ ፡ መርማሪ ፡ መሐንዲስ ፡ እንዲያሳያቸው ፡ እየተማከሩ ፡ ይሠራሉ ።

### ዐሥራ ፡ አራተኛ ።

ብዙ ፡ ዛፍ ፡ ያላሥራት ፡ እንዳይቈረጥ ፡ ያገር ፡ ሜካ ፡ ይጠብቃል ፤ አገር ፡ ይደርቃልና ፤ ሰውንም ፡ ያዛል ፡ ትንንሽ ፡ ዛፎች ፡ እንዳይነኩ ፤ የሚቈረጠውን ፡ የትልልቅ ፡ ዛፎች ፡ ቍጥር ፡ ይወስናል ። ከነገሮችም ፡ ጋራ ፡ ተማክረው ፡ ርሳቸውም ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ ይጠብቃሉ ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ አሉና ፤ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ዛፍ ፡ ለተከለ ፡ ሰው ፡ ደስታ ፡ ይሰጣል ።

### ዐሥራ ፡ አምስተኛ ።

ንጉሥ ፡ ያዘዙትን ፡ የርሻ ፡ ገበሬ ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ።

### ዐሥራ ፡ ስድስተኛ ።

እርሱ ፡ ነው ፡ የመሬት ፡ ግብር ፡ የከብት ፡ ግብር ፡ የመሥሪያ ፡ ቤት ፡ ግብር ፡ የሚያቆም ። ባመት ፡ ባመት ፡ የዚህን ፡ ግብር ፡ መዝገብ ፡ ነገሮችን ፡ ይጠይቃል ፤ ሒሳቡን ፡ እንዲያስብበት ። ካሰበ ፡ ድምሩንም ፡ ከደመረ ፡ በኋላ ፡ መዝገቡን ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይሰጣል ።

## <u>የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሚኒስቴር ፡ ደንብ ፡ (ዝክረ ፡ ነገር</u> ፡ ገጽ ፡ ፩፻፹፮—፻፹፯)

### መዠመሪያ ።

ስለ ፡ መንግሥት ፡ የሚሆን ፡ ሥራ ፤ እንደ ፡ መንገድ ፤ ምድር ፡ በባቡር ፡ ድልድይ ፤ መሽረብ ፡ ለሌላ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የርሱ ፡ ደንብ ፡ ነው

### ሁለተኛ ።

ስለ ፡ መንግሥት ፡ ቤት ፡ ሲሠራ ፡ ሥራውን ፡ ደኅና ፡ ሆኖ ፡ እንዲሠራ ፡ ይጠብቃል ፤ ከመሐንዲሶችና ፡ ከሠራተኞች ፡ ጋራ ፡ ኮንትራት ፡ አድርጎ ፡ ያትማል ።

### ሦስተኛ ።

የመንግሥት ፡ መንገድ ፡ ድልድይ ፡ ቤት ፡ ሁሉንም ፡ ያስጠብቃል ፤ የተበላሸ ፡ እንደሆነ ፡ ያስበጃል ።

### አራተኛ ።

የሚቈረጥ ፡ ዛፍ ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቃል ፤ ይህ ፡ ሥራ ፡ የመንግሥት ፡ ሲሆን ፡ ጊዜ ፡ ዕንጨት ፡ ለመውሰድ ።

### አምስተኛ ።

ውል ፡ ያላቸውን ፡ ያስጠብቃል ፤ ዕንጨት ፡ የሚቈርጡትን ፡ የመሽረብ ፡ ውሃ ፡ የሚሸጡትን ።

## ስድስተኛ ።

ግድብ ፡ ቢታላቅ ፡ ወንዝ ፡ ስለ ፡ መስኖ ፡ ያስበጀል ፤ ከርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋራ ፡ ሥራውን ፡ አስተውለው ፡ እየተስማሙ ።

## ሰባተኛ ።

ስለ ፡ ኮንትራት ፡ ያለውን ፡ ይጠብቃል ፤ በውላቸው ፡ የተጻፈ ፡ ነገር ፡ እንዲ ይተላለፍ ።

## ስምንተኛ ።

ርሱ ፡ ነው ፡ የምድር ፡ ባቡር ፡ መርማሪ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ የሚያሠራ ውን ፡ ሁሉ ።

## ዘጠነኛ ።

ሰውን ፡ ገንዘብ ፡ የሚያስከፍሉበትን ፡ ድልድይ ፡ ወይም ፡ መንገድ ፡ የርሱ፡ ምስለኔዎች ፡ በርሱ ፡ ቃል ፡ ይጠብቃሉ ፤ ያስከፍላሉ ።

## ዐሥረኛ ።

የሀገር ፡ ግዛት ፡ መኳንንት ፡ በሀገራቸው ፡ ይህነን ፡ ግብር ፡ በሚኒስቴሩ ፡ ፊንታ ፡ ይከፍላሉና ፡ ባመት ፡ ባመት ፡ የሰበሰቡትን ፡ ይልኩለታል ።

## ዐሥራ ፡ አንደኛ ።

ይህ ፡ ሚኒስቴር ፡ የተቀበለውን ፡ ግብር ፡ ለመንግሥት ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ይሰጣል ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋራ ።

## ዐሥራ ፡ ሁለተኛ ።

የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የዕቃ ፡ መቀመጫ ፡ ይጠብቃል ፤ ባመት ፡ መጨረሻ ፡ የዕቃውን ፡ ቍጥር ፡ መዝገቡንም ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያሳልፋል ።

## <u>የገንዘብና ፡ የጓዳ ፡ ሚኒስቴር ፡ ደንብ ፡</u> (ዝክረ ፡ ነገር ፡ ገጽ ፡ ፪፻፷—፪፻፶፱)

ይህ ፡ ሚኒስቴር ፡ የመንግሥት ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ዋና ፡ ጠባቂ ፡ ነው ፡ የሱ ፡ ሥራ ፡ ይህ ፡ ነው ።

## መጀመሪያ ።

የመንግሥት ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ የንጉሥ ፡ የራሳቸው ፡ ግምጃ ፡ ቤትና ፡ የን ጉሥ ፡ ያልጋቸው ፡ ገንዘብ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ።

## ሁለተኛ ።

የንጉሥ ፡ የራሳቸውና ፡ ያልጋቸው ፡ ግምጃ ፡ ቤትን ፡ ይጠብቃል ።

(ሀ) የራሳቸውን ፡ ከራሳቸው ፡ በኋላ ፡ ወራሻቸው ፡ ይወርሳቸዋል ፤ ደግሞ፡ በደብዳቤ ፡ ለእብያተ ፡ ክርስቲያናት ፤ ለበሽተኛ ፡ ቤቶች ፤ ለምጿት ፡ ወይም ፡ ለሰው ፡ ስጦታ ፡ መስጠት ፡ ይችላሉ ።

(ለ) የግላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ግን ፡ በሕይወታቸው ፡ የርሳቸው ፡ ገንዘብ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግር ፡ ከርሳቸው ፡ በኋላ ፡ አዲሱ ፡ ንጉሥ ፡ ይወርሳል ።

## ሦስተኛ ።

የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ስላገር ፡ ግዛትና ፡ ስለ ፡ መንግሥት ፡ ሥራ ፡ ነው ።

### አራተኛ ።

የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ በባንክና ፡ በሌላ ፡ ገንዘብ ፡ ቤት ፡ የመንግሥት ፡ ምስለኔ ፡ ነው ።

### አምስተኛ ።

ርሱ ፡ ያገር ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ ነው ፡ የ ቼያሾማቸው ፡ በንጉሡ ፡ ቃል ።

### ስድስተኛ ።

የመንግሥትን ፡ ገቢ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ማኅኖቹ ፡ ይሰበስባል ፤ የሌላ ፡ ሚኒስቴር ፡ ገቢ ፤ የግዛትም ፤ የትልልቆችም ፡ ቤቶች ፡ የባንኮችም ፤ የሞኖፖልም ፤ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤትም ፡ ሌሎችም ፡ ወደ ፡ ገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሲገባ ፡ ከደብተሩ ፡ ጋራ ፡ ይገባል ። ደብተሩም ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ቤት ፡ እማኆን ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣል ፤ ሚኒስቴሩም ፡ ተቀበልኩ ፡ የሚል ፡ ወረቀት ፡ ይሰጣል ።

### ሰባተኛ ።

የመንግሥት ፡ ወጪ ፡ ሁሉ ፡ ከገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ማኆን ፡ ይወጣል ፤ ተቀበልኩ ፡ የሚል ፡ ወረቀት ፡ እየተቀበለ ።

### ስምንተኛ ።

ብዙ ፡ ገቢና ፡ ወጪ ፡ ሲዠመር ፡ በአምስቱ ፡ መዠመሪያ ፡ ቀን ፡ መጨረሻ ፡ ነው ።

### ዘጠነኛ

ሚኒስቴሮቹ ፡ ወር ፡ ሲገባ ፡ እስከ ፡ ፭ኛ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ደብተሩን ፡ ደምረው ፡ ወደ ፡ ገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይልካሉ ። የተረፈውን ፡ ያገባሉ ፤ ወይም ፡ ያነሰውን ፡ ይከፍላሉ ።

### ዐሥረኛ ።

ከብዙ ፡ ገቢና ፡ ወጪ ፡ ነገር ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ወጪ ፡ አለ ፡ ንጉሥ ፡ የሚያዙት ። ስለዚህ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ዘወትር ፡ ክፍት ፡ እንዲሆን ፡ ይገባል ፡ በቀን ፡ በቀን ፡ ፬ ፡ ሰዓት ፤ ከሰንበትና ፡ ከበዓላት ፡ ቀን ፡ በቀር ።

### ዐሥራ ፡ አንደኛ ።

የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነው ፡ በመንግሥትና ፡ በነጋዴ ፡ የመንግሥት ፡ አሰናጂዎች ፡ መካከል ፡ ውል ፡ የሚያደርግ ፤ ሲመች ፡ ኀራጅ ፡ ያደርጋል ።

### ዐሥራ ፡ ሁለተኛ ።

ለፈረንጆች ፡ የሚሰጥ ፡ ውል ፤ ሞኖፖል ፤ እርሻ ፡ ሌሎች ፤ ለገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ማስታወቅ ፡ ነው ። የመንግሥት ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ጠባቂ ፡ ነው ።

### ዐሥራ ፡ ሦስተኛ ።

የመንግሥት ፡ ስሌት ፡ ደብተር ፡ ሁሉ ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ እጅ ፡ እንዲሆን ፡ ነው ።

### ዐሥራ ፡ አራተኛ ።

የመንግሥት ፡ ስሌት ፡ ደብተር ፡ ዕጥፍ ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል ። ስለ ፡

ምን ፡ እንዱ ፡ ቢጠፋ ፡ እንዱ ፡ ይጸናል ፤ ሒሳቡም ፡ ሲፈለግ ፡ ይገኛል ።

## ዐሥራ ፡ አምስተኛ ።

የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ በ፫ ፡ ወር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የመንግሥት ፡ ሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ያደርጋል ። ደግሞ ፡ የዳር ፡ አገር ፡ ግምጃ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ ደብተራቸውን ፡ ይደምራሉና ፡ ወደ ፡ ገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይልካሉ ፤ ከሒሳባቸውም ፡ የ፫ ወር ፡ ቀሪ ፡ ይጽፋሉ ፡ የግምጃ ፡ ቤታቸውን ፡ ብር ፡ ሁሉ ።

## ዐሥራ ፡ ስድስተኛ ።

በዓመት ፡ መጨረሻ ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ማድረግ ፡ ነው ፤ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስሌቱን ፡ ማስቀመጥና ፡ ለንጉሥ ፡ ለመማክርቱ ፡ ማኅበር ፡ ማሳየት ፡ ነው ።

## ዐሥራ ፡ ሰባተኛ ።

የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ወደ ፡ ዳር ፡ አገር ፡ መርማሪ ፡ መስደድ ይችላል ፤ ይህ ፡ መርማሪ ፡ የግምጃ ፡ ቤቶችን ፡ ሣጥንና ፡ መዝገብ ፡ ይመረምራል ።

## ዐሥራ ፡ ስምንተኛ ።

በዓመት ፡ መጨረሻ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የንዳ ፡ ዕቃ ፡ ቁጥሮ ፡ በመዝገብ ፡ ይጽፋል ፤ ዕቃውን ፡ በያይነቱ ፡ በ፩ ፡ ልዩ ፡ መዝገብ ፡ ይጽፋል ፤ ደግሞ ፡ ለመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሚኒስቴር ፡ የቃ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ይጠይቃል ።

## ዐሥራ ፡ ዘጠነኛ ።

የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ባመት ፡ መጨረሻ ፡ መዝገቡን ፡ ደምረው ፡ የሌላ ፡ ሚኒስቴሮችን ፡ መዝገብ ፡ ጨምረው ፡ የመንግሥት ፡ ይደረጋል ።

## ኻያኛ ።

ዓመት ፡ ከተጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ገቢና ፡ ወጪ ፡ ከተደመረ ፡ በኋላ ፡ የተረፈውን ፡ ብር ፡ በሣጥን ፡ ለብቻ ፡ ያስቀምጡታል ፤ ይህ ፡ ሣጥን ፡ የመንግሥት ፡ ድልብ ፡ ይሆናል ። ለዚህም ፡ ለድልብ ፡ ሣጥን ፡ አንድ ፡ እለቃ ፡ ለብቻ ፡ ይደረግለታል ፡ መዝገቡ ፡ ለብቻ ፡ ነውና ፡ ከዚህም ፡ ሣጥን ፡ ሲያወጡ ፡ ለማኅበር ፡ መማክርት ፡ ማስታወቅ ፡ ነው ።

## ኻያ ፡ አንደኛ ።

በክፉ ፡ ዓመት ፡ ድንገት ፡ ገቢ ፡ ከወጪ ፡ ያነሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መንግሥት ፡ ከድልብ ፡ ሣጥኑ ፡ ያወጣል ፤ ክፉ ፡ ዓመት ፡ ማለት ፡ ጦርነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ወይም ፡ ረኃብ ፡ ወይም ፡ "ኮሌራ" ወይም ፡ ክፉ ፡ ሌላ ፡ በሽታ ።

## ኻያ ፡ ሁለተኛ ።

ድንገት ፡ ገንዘብ ፡ የተበደረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራበት ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነው ፡ ይህንን ፡ ብድር ፡ የሚጠብቅ ፤ ወለዱ ፡ ባመት ፡ ባመት ፡ ይሰጣልና ፡ ዋና ፡ ገንዘቡን ፡ ይከፍላል ፤ ለብድሩ ፡ ውል ፡ ተብሎ ፡ እንደ ተጻፈ ።

## ኻያ ፡ ሦስተኛ ።

ከገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሣጥን ፡ የሚወጣና ፡ የሚገባ ፡ ብር ፡ በባለ ፡ ዕጥፍ ፡ ወረቀት ፡ ደብተር ፡ ይጻፋል ፤ እንዱን ፡ ወረቀት ፡ ቀደው ፡ እንሥተው ፡ ሁለተ

ኛው ፡ በመዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ይቀራል ፤ በ፪ኛ ፡ ወረቀት ፡ የተጻፈው ፡ ቃል ፡ አንድ ይሆናል ።

ካያ ፡ አራተኛ ።

የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ መዝገቦች ፡ ሁሉ ፡ ሒሳባቸው ፡ በልክ ፡ እንዲሆን ፡ የመንግሥት ፡ ስሌት ፡ ልክ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መንግሥቱ ፡ ኪሳራ ፡ ይገ ባል ።

ካያ ፡ አምስተኛ ።

ንጉሥ ፡ የመንግሥት ፡ ማኅበርም ፡ መማክርት ፡ እንዲያደርጉ ፡ ብለዋል ፤ ይህ ፡ ማኅበር ፡ ሲሰበሰብ ፡ በስብከት ፡ ገና ፡ ጊዜ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለዚህ መማክርት ፡ ያገር ፡ ሀብት ፡ ማሳየት ፡ ያስፈልጋል ።

ካያ ፡ ስድስተኛ ።

የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥራውን ፡ እንደዚሁ ፡ ይከፍላል ፤ ለየክፍሉ ፡ አንዳ ንድ ፡ አለቃ ፡ እያደረገ ።

፩ኛ ፤ የግብርና ፡ የጉምሩክ ፡ ክፍል ።
፪ኛ ፡ የጽሕፈት ፡ ክፍል ።
፫ኛ ፤ የግምጃ ፡ ቤት ፡ ክፍል ።
፬ኛ ፤ የባንኮች ፡ ክፍል ።
፭ኛ ፤ የድልብ ፡ ማጥን ፡ ክፍል ።
፮ኛ ፡ የልብስና ፡ የጌጥ ፡ ዕቃ ፡ ክፍል ።
፯ኛ ፤ የጓዳ ፡ ክፍል ፡ ከልብስና ፡ ከጌጥ ፡ በቀር ።

ለየክፍሉ ፡ አንዳንድ ፡ ልዩ ፡ ማኅተም ፡ ይደረጋል ። ስለ ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፤ ስለቁም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሚኒስቴሩ ፡ ማኅተም ፡ ያስፈልጋል ።

የዳኝነት ፡ ሚኒስቴር ፡ ደንብ ፡ (ዝክረ ፡ ነገር ፡ ገጽ ፡ ፹፩—፹፪)

መዠመሪያ ።

ይህ ፡ ሚኒስትር ፡ ያገር ፡ ዳኞች ፡ ዋና ፡ አለቃ ፡ ነው ።

ሁለተኛ ።

የሚፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ሁሉ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ቃል ፡ በትጋት ፡ የሚ ጠብቅ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ሦስተኛ ።

የሚፈርደውን ፡ ባገርም ፡ የሚፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ሁሉ ፡ በመዝገብ ፡ ያጽ ፋል ።

አራተኛ ።

በየሻለቆችም ፡ አገር ፡ ያሉትን ፡ ዳኞች ፡ ሁሉ ፡ የፍርዳቸው ፡ መዝገብ ፡ ግልባጭ ፡ ባመት ፡ ባመቱ ፡ ወደሱ ፡ እየመጣ ፡ ይታያል ።

የጦር ፡ ሚኒስቴር ፡ ደንብ ፡ (ዝክረ ፡ ነገር ፡ ገጽ ፡ ፪፻፹፫—፪፻፹፬)

መዠመሪያ ።

የጦርነት ፡ ሚኒስቴር ፡ የንጉሥ ፡ ሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ነው ፤ ወታደር ፡ በየጭ

ፍራው ፡ እንዲቀመጥ ፡ ሰራዊት ፡ ሁሉም ፡ የጦርነት ፡ ትምህርት ፡ እንዲማር ፡ ይጠብቃል ፨

ሁለተኛ ፨

የጦር ፡ ነገር ፡ ለማሰናዳት ፡ የንጉሥን ፡ ቃል ፡ ይጠብቃል ፨

ሦስተኛ ፨

የጥይት ፡ ቤት ፡ የጠመንዣ ፡ ቤት ፡ የሰራዊት ፡ ጐተራ ፡ መጠበቅ ፡ በርሱ ፡ እጅ ፡ ይሆናል ፨

አራተኛ ፨

በመንግሥትና ፡ በጭፍሮች ፡ መካከል ፡ ይሆናል ፤ ስለ ፡ ወታደር ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ዳኝነታቸውም ፡ ነገር ፨

አምስተኛ ፨

የሸዋ ፡ ጭፍሮች ፡ ተቆጣጣሪ ፡ ርሱ ፡ ነው ፤ ደግሞ ፡ የገዢዎችም ፡ ሰራዊት ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ የጦርነት ፡ ሥርዓት ፡ ሲለወጤ ፨

ስድስተኛ ፨

ጦርነት ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በርሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ፡ የአገር ፡ ሠራዊት ፡ የሚነሡ ፨

ሰባተኛ ፨

ጭፍሮች ፡ በሚያልፉበት ፡ ቦታ ፡ ድርጎ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ያዛል ፨

ስምንተኛ ፨

ያንድ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ የተነሡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዚሀ ፡ አገር ፡ ገዢ ፡ ዕርቅ ፡ ለማድረግ ፡ ያልተቻለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትር ፡ ጭፍራ ፡ አምጥቶ ፡ አገሩን ፡ ይከባል ፤ ይገባበታልም ፤ እስኪያሸንፈው ፡ ድረስ ፤ ስለዚህ ፡ ካገሩ ፡ ገዢ ፡ ይስማማል ፡ እንዲረዳው ፨

ዘጠነኛ ፨

ድንገት ፡ ስለ ፡ ጦርነት ፡ ንጉሥ ፡ ግብር ፡ ያዘዙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጦርነት ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥራ ፡ ነው ፤ ያገር ፡ ግዛትና ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ይረዱታል ፨

<u>የጤና ፡ ሚኒስቴር ፡ ደንብ ፡ (ዝክረ ፡ ነገር</u> ፡ ገጽ ፡ ፯፻፬—፯፻፮)

መዠመሪያ ፨

ይሀ ፡ ሚኒስቴር ፡ የሰውና ፡ የከብት ፡ ሁሉ ፡ ዋና ፡ ጠባቂ ፡ ነው ፨

ሁለተኛ ፨

ታላቅ ፡ በሽታ ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ እንዳይገባ ፡ ወይም ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ያለውን በሽታ ፡ ለማጥፋት ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነገር ፡ ለመንግሥት ፡ ያመለክታል ፤ መንግ ሥት ፡ ያገሩን ፡ ታላቅ ፡ በሽታ ፡ ያልከለከለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌሎች ፡ መንግሥ ቶች ፡ በሽታ ፡ ያለበትን ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ከብት ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ይከልክሉ ፤ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ እንዳይገባ ፡ ውል ፡ አለ ፡ መንግሥቶች ፡ ሁሉ ፡ መከልከል ፡ ስለዚሁ ነገር ፨

ሦስተኛ ።

ያገር ፡ ጥራት ፡ ያስጠብቃል ፡ የሰውም ፡ ጤና ፡ ደኅና ፡ እንዲሆን ፡ ያስመረ ምራል ።

አራተኛ ።

ያገር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ ተቈጣጣሪ ፡ ይሆናል ፤ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንዳ ይሆንባቸው ፡ የሰው ፡ ጤና ፡ የሚያስጐዳ ።

አምስተኛ ።

ማንም ፡ የመሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለመክፈት ፡ መንግሥት ፡ አይፈቅድለትም ፡ የጤና ፡ ሚኒስቴር ፡ አይቶ ፡ አስተውሎ ፡ ቃሉን ፡ ሳይሰጥ ፤ ይህ ፡ የመሥሪያ ፡ ቤት ፡ በዕቃው ፡ ወይም ፡ በቦታው ፡ ምክንያት ፡ ለሰው ፡ ጤና ፡ ክፋትም ፤ የሰ ውም ፡ ብሎ ፡ ለመንግሥት ፡ ያመልክት ።

ስድስተኛ ።

የመንግሥት ፡ ሐኪሞች ፡ ሁሉ ፡ ለርሱ ፡ ይታዘዛሉ ፤ በርሱ ፡ ምክር ፡ ነው መንግሥት ፡ የሚሾማቸው ።

ሰባተኛ ።

የበሽተኛ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ ተቈጣጣሪ ፡ ይሆናል ፤ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ቢሆን ፡ ወይም ፡ ለሌሎች ፡ መንግሥቶች ፡ ወይም ፡ ለሌላው ፡ ሰው ።

ስምንተኛ ።

የሀገር ፡ በሽተኛ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ የሚከፈቱት ፤ አስ ቀድሞ ፡ የዚህ ፡ በሽታ ፡ ቤት ፡ ሥዕልና ፡ ቦታ ፡ ተመልክቶ ።

ዘጠነኛ ።

ማንም ፡ ሐኪም ፡ ወይም ፡ የመድኀኒት ፡ ቀማሚ ፡ ባገር ፡ ቤት ፡ ከፍተው ፡ መድኀኒት ፡ ለማድረግ ፡ አይፈቀድላቸውም ፡ የጤና ፡ ሚኒስቴር ፡ የምስክር ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ አይቶ ፡ ካተመ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ሥራቸውን ፡ እንዲቆጣጠር ፡ ይገባዋል ።

ዐሥረኛ ።

እነዚህ ፡ ሐኪሞችና ፡ መድኃኒቶች ፡ በታላቅ ፡ ኃጢአት ፡ የተያዙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጤና ፡ ሚኒስቴር ፡ ተመልሰው ፡ መድኀኒት ፡ እንዳያደርጉ ፡ ይከለክላቸ ዋል ፤ በደላቸው ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካገር ፡ በመንግሥት ፡ ቃል ፡ እን ዲያስወጣቸው ፡ ይችላል ።

ዐሥራ ፡ አንደኛ ።

የጤና ፡ ሚኒስቴር ፡ ደግሞ ፡ የከብት ፡ ሐኪሞች ፡ አለቃ ፡ ነው ።

ዐሥራ ፡ ሁለተኛ ።

ለኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ ሐኪሞች ፡ ሁሉም ፡ ያገር ፡ ጤና ፡ ነገር ፡ ባስፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ያስታውቃል ፤ እርሱም ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ይሰበስባል ።

## ዐሥራ ፡ ሰስተኛ ።

በኢትዮጵያ ፡ በሌላ ፡ መንግሥት ፡ መካከል ፡ ውል ፡ ለማድረግ ፤ ስለ ፡ ጤና ፡ ነገር ፡ የሚያስፈልግ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የጤናና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሚኒስትሮች ፡ ተማክረው ፡ አብረው ፡ ውሉን ፡ ይጽፋሉና ፡ ክፉ ፡ እንዳይሆን ።

<u>የጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ፡ (ማኅተም፡ጠባቂ) ደንብ (ዝክረ ፡ ነገር ፡ ገጽ ፡ ፮፻፵፮)</u>

## መግመሪያ ።

ይህ ፡ ሚኒስቴር ፡ የንጉሥ ፡ ጸሐፊዎች ፡ አለቃ ፡ ነው ፤ ሥራው ፡ በንጉሥ፡ ቤት ፡ ነው ።

## ሁለተኛ ።

ከንጉሥ ፡ ቤት ፡ የሚጻፈውን ፡ ወረቀት ፡ ሁሉ ፡ በታላቅ ፡ መዝገብ ፡ ይገለብጣል ፤ ከንጉሥ ፡ ቤት ፡ በመዝገብ ፡ የማይገለበጥ ፡ ወረቀት ፡ ሁሉ ፡ ከቶ ፡ እንዳይወጣ ።

## ሦስተኛ ።

የወረቀት ፡ ግልባጭ ፡ ሁሉ ፡ የዱሮ ፡ መጻሕፍትንም ፡ በመንግሥት ፡ ማኅ ን ፡ ይጠብቃል ።

## አራተኛ ።

የኒሻን ፡ ነገር ፡ የርሱ ፡ ሥራ ፡ ነው ።

## አምስተኛ ።

የመንግሥት ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ አለቃ ፡ እርሱ ፡ ነው ።

<u>አባሪ ፡ ፫ ፡ በምኒልክ ፡ ስለተቋቋሙት ፡ ሚኒስቴሮች ፡ በምሳሌ ፡ የቀረበ ፡ ጽሑፍ ።</u>

<u>በምሳሌና ፡ በትርጓሜ ።</u>

ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተስማሚ ፡ የምክር ፡ ጽሑፍ ፡ ሀገሩንና ፡ መንግሥቱን ፡[1] ለወደደ ፡ ሁሉ ፡ ተጻፈ ።

ከኢትዮጵያ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ማኀተሚያ ።

ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ለትልቅ ፡ ትንሹ ፡ የምኒስቴሮችን ፡ ሥራ ፡ በምሳሌ ፡ ለማስታወቅ፡ ደግሞ፡የምንስቴሮች፡ሥራ፡መንግሥትንና፡ሕዝብን፡አንድ፡ልብ፡አንድ፡ ፈቃድ ፡ ለማድረግ ፡ ኃይል ፡ እንዳለው ፡ ለማስረዳት ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ፲፰፻፹ ፡ ዓመት ፡ ምኅረት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ታተመ ።

ለተወደዱ ፡ ክቡራን ፡ ሚኒስቴሮች ፡ እውቀትን ፡ ለመጨመርና ፡ ለማብዛት ፡ አልደፈርሁም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እውቀትን ፡ ለናፈቁ ፡ ልጆች ፡ መንግሥትን ፡

1. የተርጓሚ፡ማስታወሻ፡መንግሥት፡የሚለው፡ከግዕዝ፡የተገኘ፡የአማርኛ፡ቃል፡እንደአገባቡ ፡ ንጉሥ ፡ ወይም፡መንግሥት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡ ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሐዲስ (፲፱፻፵፰) ፡ በሚለው ፡ የኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፮፻፹፭ ፡ ይመለከቷል ።

በራስ ፡ ምንስቴሮችን ፡ ባካላት ፡ መስዬ ፡ የልቤን ፡[2] አሳብ ፡ ለመግለጥ ፡ እጽፋ ለሁ ።

መምሬ ፡ ብሥራት ፡ ዘብሔረ ፡ መንዝ ።

አገሩንና ፡ መንግሥቱን ፡ የወደደ ፡ ሰው ፡ አሳብ ፡ ይህ ፡ ነው ።

የውቀት ፡ መንፈስ ፡ ያደረበት ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማኅበር ፡ ምሳሌ ፡ አድርጎ ፡ የጻፈውን፡እኔም፡እሱን፡ መሠረት ፡ አድርጌ።የቤተ ፡ መን ግሥትን ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ ባንድነት ፡ ሳሉ ፡ ለየራሱ ፡ ሊሠራ ፡ የሚችለውን ፡ በዚያው ፡ ምሳሌ ፡ እጽፋለሁ ።

ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ችሎት ፡ በሰፊ ፡ ዕውቀታቸው፡ እንደ ፡ ብልሐተኛ ፡ መሐንዲስ ፡ መሠረት ፡ አስቀመጡ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ የሥራውን ፡ ነገር ፡ ይመልከት ። ማንም ፡ አይችልምን ፡ ሌላ ፡ መሠ ረት ፡ ይመሠርት ፡ ዘንድ ፡ ከዚያው ፡ ከተመሠረተው ፡ ከወራሹ ፡ ከልጅ ፡ ኢያሱ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ቢሠራ ፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ይጸናለ ታል ። ሥራውም ፡ የጸናለት ፡ ዋጋውን ፡ ይቀበላል ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ፡፲፩ና፡ ፲፬ ፡[3]

የማገልገል ፡ ሥራ ፡ ልዩ ፡ ልዩነት ፡ አለው ፡ ሰጭው ፡ እግዚንብሔር ፡ ግን፡ አንድ ፡ ነው ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፭ ፡[4] እንዲሁ ፡ በተፈጥሮ ። ከራስ ፡ ጸጉ ራችን ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጥፍራችን ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይባ ላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ ውስጥ ፡ በስምና ፡ በሥራ ፡ ብዙ ፡ ልዩነት፡ያላቸው፡ አሉ ።

በስም ፡ እነዚሁ ፡ ናቸው ። ራስ ፤ ጉሮሮ ፤ አፍንጫ ፤ ዓይን ፤ አፍ ፤ ልብ ፤እጅ፤ እግር ፤ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ አለ ።

እነዚህም ፡ በሥራ ፡ ልዩ ፡ ናቸው ።

## የራስ ፡ ሥራ ።

በነፍስና ፡ በሥጋ ፡ ባጥንትና ፡ በኸርማት ፡ ተዋደው ፡ በሚኖሩ ፡ አካላት ፡ ሁሉ ፡ አለቃና ፡ የውቀት ፡ መሰብሰቢያ ፡ ግጥን ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የቀሩትን ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ፡ ኤፌ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፲፭ና ፡ ፲፮ ።[5]

---

2. የተርጓሚ ፡ ማስታወሻ ፡ ልብ ፡ የተወሰደው ፡ እንደማሰቢያ ፡ የአካል ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ (ማቴዎስ ፡ ፲፪ ፤ ፴፩) ፡ በተጨማሪም ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ኪዳን ፡ ወልድ ፡ ክፍሉን ፡ ይመለከቷል ።

3. "፲ ፡ እንደ ፡ ተሰጠኝ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ መሠረት ፡ አስቀመጥሁ ፡ እንደ ፡ ብልሀ ተኛ ፡ አናጺ ። ሌላውም ፡ በላይ ፡ ይሠራል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ይመልከት ፡ እን ዴት ፡ በላይ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ። ፲፩ ማንም ፡ አይችልምና ፡ ሌላ ፡ መሠረት ፡ ይመሠረት ፡ ዘንድ፡ ከዚያ ፡ ከተመሠረተው ፡ በቀር ፡ እርሱም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። — — — — ፲፬ የሥራው ሰራ ፡ የጸናለት ፡ ሰው ፡ ዋጋውን ፡ ይወስዳል ።"

4. "፭ ለማገልገልም ፡ ልዩነት ፡ አለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ አንድ ፡ ነው ።"

5. "፲፭ በፍቅር ፡ ግን ፡ እውነተኞች ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ ወደርሱ ፡ ራሱ ፡ ወደሚሆን ፡ እንድናድግ ፡ እርሱም ፡ ክርስቶስ ። ፲፮ ሥጋ ፡ ሁሉ ፡ የሚዋደድበት ፡ በጅማትም ፡ ሁሉ ፡ የሚስማማበት ፡ የሚታወርም ፡ እያንዳንዱ ፡ በየክፍሉ ፡ የተሰጠውን ፡ ያህል ። ሥጋ ፡ እንዲያድግበት ፡ በፍቅር ፡ ይሰራ ፡ ዘንድ ።"

## የጕሮሮ ፡ ሥራ ።

ጕሮሮ ፡ በትምህርት ፡ የሚገኘውን ፡ ጥበብና ፡ ዕውቀት ፡ ሁሉ ፡ ከራስና ፡ ከልብ ፡ ለማዋኀድ ፡ የድምጽ ፡ ኀይል ፡ የሚስብ ፡ መኪናነት ፡ አለው ።

ጕሮሮ ፡ ባይኖር ፡ ዕውቀትና ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ ንግግር ፡ ባልተገኘም ፡ ነበር ። እንደ እንስሳ ፡ መሆን ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የቀሩትን ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ።

## ያይን ፡ ሥራ ።

ዓይን ፡ ለማየት ፡ ከብርሃን ፡ ጋራ ፡ ተስማምቶ ፡ የተፈጠረ ፡ ያካላት ፡ ሁሉ ፡ መብራት ፡ ነው ። በጅና ፡ በግር ፡ ለሚሠራ ፡ ሥራ ፡ በትምህርት ፡ ለሚገኝ ፡ ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ መሪ ፡ ነው ፡ ግዙፍ ፡ ሆኖ ፡ የተፈጠረውን ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ለማየት ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን፡የቀሩትን ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ፡ ማቴ ፡ ፮ ፡ ፳፪ ።[6]

## ያፍንጫ ፡ ሥራ ።

አፍንጫ ፡ የሕይወታችን ፡ ትንፋሽ ፡ መመላለሻ ፡ ደግና ፡ ክፉ ፡ ማሽተቻ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የቀሩትን ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ፡ ዘፍጥ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፯[7]

## ያፍ ፡ ሥራ ።

አፍ ፡ ደግና ፡ ክፉ ፡ የታዘዘውን ፡ ያልታዘዘውንም ፡ መናገሪ ። መብሊያ ፡ መጠጫ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የቀሩትን ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ።

## የልብ ፡ ሥራ ።

ልብ ፡ የደግና ፡ የክፉ ፡ አሳብ ፡ ሁሉ ፡ መብቀያ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የቀሩትን ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ፡ ማቴዎስ ፡ ፲፱ ፡ ፴፭ ።[8]

## የሆድ ፡ ሥራ ።

ሆድ ፡ የመብልና ፡ የመጠጥ ፡ ማከማቻ ፡ በአካል ፡ ውስጥ ፡ ባለ ፡ ሥር ፡ ሁሉ ፡ ቅባት ፡ ቅባቱን ፡ የሚነዛ ፡ እሥሩን ፡ የሚጥል ፡ ነው ። ሥጋችን ፡ ካልበላ ካልጠጣ ፡ ደም ፡ አይሰጥምና ፡ ደምም ፡ ከሌለ ፡ ነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ ትለያለች ። ነገር ግን ፡ የቀሩትን ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ። የሐዋ ፡ ም ፡ ፳፯ ፡ ቍ ፡ ፴፬ ።[9]

## የጅ ፡ ሥራ ።

እጅ ፡ በጥበብ ፡ ለተገኘ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የብረትና ፡ የናስ ፡ የወርቅ ፡ ፋብሪካና ፡ መኪና ፡ በያይነቱ ። የርሻ ፡ የጽፈት ፡ የስፌት ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ በያይነቱ ። ይህን ፡ ለመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ሠራተኛ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የቀሩትን ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡

---

6. "፳፪- የሥጋ ፡ መብራት ፡ ዓይን ፡ ነው ። ዓይንህም ፡ ጥሩ ፡ ብትሆን ፡ ሥጋህ ፡ ሁሉ ፡ የበራ ፡ ይሆናል ።"

7. "፯- እግዚአብሔርም ፡ አምላክ ፡ ሰውን ፡ ፈጠረ ፡ መሬት ፡ ከምድር ። በፍንጫውም ፡ የሕይወት ፡ እስትንፋስ ፡ እፍ ፡ አለበት ። ሰውም ፡ ሕይወት ፡ ያለበት ፡ ነፍስ ፡ ሆነ ።"

8. የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፱ ፡ ቍጥር ፡ ፴፭ ፡ የሚል ፡ ስሌለ ፡ ጸሐፊው ፡ የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፪ ፡ ቍጥር ፡ ፴፭ን ፡ መጥቀሳቸው ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ገምተናል። እሱም ፡ እንዲህ፡ ይላል ፡ "፴፭- መልካም ፡ ሰው ፡ ከመልካም ፡ ልቡ ፡ መዝገብ ፡ መልካም ፡ ያወጣል ። ክፉም ፡ ሰው ፡ ከክፉ ፡ መዝገቡ ፡ ክፉ ፡ ያወጣል ።"

9. "፴፬- ስለዚህም ፡ እለምናችኋለሁ ፡ መብል ፡ ትወስዱ ፡ ዘንድ ፡ እርሱ ፡ ለመድኃኒታችሁ ፡ ይሆንላችኋልና ። ከላንትም ፡ ከራስ ፡ አንዲት ፡ ጸጉር ፡ ስንኳ ፡ አትወድቅም ።"

አይችልም ፡ የሐዋ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ ፡ ፴፬ ። ፩ ፡ ተሰ ፡ ምዕ ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፱ ።[10]

## የግር ፡ ሥራ ።

እግር ፡ ለነዚህ ፡ ለተቆጠሩት ፡ ሁሉ ፡ መቆሚያ ፡ ጉልበትና ፡ ብርታት ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ አሰበበትና ፡ ወደ ፡ ታዘዘበት ፡ መሔጃ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የቀሩ ትን ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ።

እነዚህንም ፡ አካላት ፡ እግዚአብሔር ፡ ባንድ ፡ ሥጋ ፡ አስማምቶ ፡ በሥራና፡ በስም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ አቆማቸው ፡ አንድ ፡ አካል ። አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይበላሉ ። ደግሞ ፡ እግር ፡ እኔ ፡ እጅ ፡ አይደለሁምና ፡ የሥጋ ፡ ወገን ፡ አልሆንም፡ ብትል ፡ ስለዚህ ፡ ከሥጋ ፡ ወገን ፡ መሆንዋ ፡ አይቀርም ። ወይስ ፡ ሁሉ ፡ ዓይን ፡ ቢሆን ። መስማት ፡ ወዴት ፡ በተገኘ ። ሁሉም ፡ ጆሮ ፡ ቢሆን ፡ ማሽተት ፡ ወ ዴት ፡ በተገኘ ። ዓይንም ፡ አይቻላትም ፡ እጅን ፡ አልሻሽም ፡ ትላት ፡ ዘንድ ። ራ ስም ፡ እግሮችን ፡ እጆችን ፡ የቀሩትንም ፡ ሁሉ ፡ አልሻችሁም ፡ ይላቸው ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ። አንዱ ፡ ቢታመም ፡ ሁሉም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ይታመማል ። አንዱ ፡ ደስ ፡ ቢለው ፡ ሁሉም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ ይለዋል ። እነዚህም ፡ ባንድ ፡ ሥጋ ፡ ተስማምተው ፡ ያሉ ፡ ብልቶች ፡ ሁሉ ፡ በስምና ፡ በሥራ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስለ ፡ ሆኑ፡ ባንድነት ፡ ራሳቸውን ፡ ጠብቀው ፡ በየሥራቸው ፡ ካልቆሙ ፡ ሁሉም ፡ አንድ ነት ፡ ጠፊ ፡ ናቸው ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ፡ ፳፮ ።[11]

## መዠመሪያ ።

መንግሥት ፡ በራስ ፡ ይመሰላል ። ይኸውም ፡ ምሳሌ ፡ እንዲህ ፡ ነው ። መንግሥት ፡ ማለት ፡ የፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ የፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ጠባቂ ። የው ቀት ፡ ሁሉ ፡ መገኛ ። የጥበብ ፡ ሁሉ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ቀጥዬ ፡ የጻፍኋቸው ፡ አካላት ፡ ምንስቴሮች ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ የቀሩትን ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ።

## ሁለተኛ ።

ምንስቴሮች ፡ በጆሮ ፡ ይመሰላሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ጆሮ ፡ ደጉንም ፡ ክፉንም ፡ ሰሚ ፡ ነው ። እሱ ፡ ነው ፡ ዕውቀትን ፡ ሁሉ ፡ የሚስብ ። ራስ ፡ ሁሉ ፡ ያለሱ ፡ እው ቀትንና ፡ ብልሐትን ፡ ለማግኘት ፡ አይችልም ። እንዲሁ ፡ መንግሥትም ፡ ብቻ ውን ፡ ያለ ፡ መካሮች ፡ ዕውቀትና ፡ ብርታት ፡ ብዙ ፡ ሐብትና ፡ ደግነት ፡ ለማግ ኘት ፡ አይችልም ።

---

10. የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ምዕራፍ ፡ ፳ ፡ ቍጥር ፡ ፴፬ ፡ እንዲህ ፡ ይላል“ ፴፬- እላንትም ፡ ታውቃላችሁ፡ እሊህ ፡ እጆቼ ፡ ለምሻው ፡ ነገር ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ላሉትም ፡ እንዳገለገሉ።። “መጀመሪያይቱ ፡ ወደ፡ ተሰሎንቄ ፡ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ቍጥር ፡ ፱ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ “፱- ድካማችንን ፡ ታስባላችሁና ፡ ወን ድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ጣራችንንም ። በሌትና ፡ በቀን ፡ እንሰራ ፡ ነበርንና ፡ ከላንት ፡ ባንዱ ፡ እንዳናከብድ እንዲሁም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወንጌል ፡ አስተማርናችሁ ።”

11. “፲፭- እግርም ፡ ብትል ፡ እኔ ፡ እጅ ፡ አይደለሁምና ፡ ከሥጋ ፡ ወገን ፡ አይደለሁም ። ስለዚህም ፡ ከሥጋ ፡ መሆንዋ ፡ ይቀራልን ። — — — —
፲፯- ሥጋ ፡ ሁሉ ፡ ዓይን ፡ ቢሆን ፡ መስማት ፡ ወዴት ፡ በተገኘ ። ሁሉም ፡ መስማት ፡ ቢሆን ፡ ወዴት ፡ በተገኘ ፡ ማሽተት ። ፳፮- አንድ ፡ ብልትም ፡ ቢታመም ፡ ብልት ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ይታመማል ። አንድ ፡ ብልትም ፡ ደስ ፡ ቢለው ፡ ብልት ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።”

## ሶስተኛ ።

ምንስቴሮች ፡ ባይን ፡ ይመስላሉ ። ዓይን ፡ ያካል ፡ ሁሉ ፡ ብርሃን ፡ ነው ። ከሰው ፡ ፍጥረት ፡ ማንም ፡ ያለ ፡ ብርሃን ፡ ለመሥራት ፡ የሚችል ፡ የለም ። እን ዲሁ ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ ምኒስቴሮች ፡ ዕውቀት ። ግዛቱን ፡ ሊያሰፋ ፡ ጠላቱን ፡ ሊያጠፋ ፡ አይችልም ። ዓይን ፡ ላካል ፡ ሁሉ ፡ ብርሃን ፡ እንደሆነ ፡ ምንስቴርም ፡ ለመንግሥት ፡ ሁሉ ፡ የውቀት ፡ ብርሃን ፡ ነው ። ዓይን ፡ ከራሱ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ እግሩ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አካላት ፡ አስተካክሎ ፡ ከብዙ ፡ ጉዳት ፡ ይጠብቃል ። እንዲሁ ፡ ምንስቴርም ፡ ከጠረፍ ፡ እስከ ፡ ጠረፍ ፡ ያለውን ፡ ሠራ ዊት ፡ ሁሉ ፡ በመንግሥትና ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ግፍና ፡ ጉዳት ፡ እንዳይገኝ ፡ አስተካክሎ ፡ ይጠብቃል ።

## አራተኛ ።

ምንስቴሮች ፡ ባፍንጫ ፡ ይመስላሉ ። አፍንጫ ፡ የአካል ፡ ሁሉ ፡ ሕይወት ፡ መመላለሻ ፡ ነው ። የመንግሥት ፡ ሕይወቱ ፡ ምኒስቴሮች ፡ ናቸው ። አፍንጫ ፡ ለአካል ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መልካም ፡ ሽታ ፡ ያቀርባል ። እንዲሁም ፡ ምን ስቴሮችም ፡ ለመንግሥት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ የመንግሥቱን ፡ ስፋት ፡ የሠራዊ ቱን ፡ ብዛት ፡ ያገሩን ፡ መልማት ፡ የሕዝቡን ፡ ዕውቀት ፡ የቀረውንም ፡ መልካም የደስታ ፡ ነገር ፡ ያቀርባሉ ። ደግሞ ፡ አፍንጫ ፡ ክፉ ፡ ሽታ ፡ ያሸተተ ፡ እንደሆነ፡ ለአካል ፡ ሁሉ ፡ በሽታ ፡ ይሆናል ፡ እንዲሁ ፡ ምኒስትሮችም ፡ ክፉ ፡ አሳብ ፡ ያሸ ተቱ ፡ (ማለት ፡ ያሰቡ) ፡ እንደሆነ ፡ ሽፍታ ፡ ወምበዴ ፡ የመንግሥት ፡ በሽታ ፡ ሁሉ ፡ ባገር ፡ ይበዛል ፡ መፈራት ፡ ይቀራል ። ሐብትና ፡ የንግድ ፡ ትርፍ ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋል ።

## አምስተኛ ።

ምንስቴሮች ፡ ባፍ ፡ ይመስላሉ ፡ አፍ ፡ ያሳብና ፡ የምክር ፡ ሁሉ ፡ መግለጫ፡ ነው ፡ ከልብ ፡ የተረፈውን ፡ አፍ ፡ ይናገራልና ፡ ምንስቴሮችም ፡ መክረው ፡ መር ምረው ፡ በመንግሥት ፡ ክፋት ፡ የተገኘበትን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ክፋቱ ፡ መጠን ፡ ፈርደው ፡ ቅጣትን ፡ ለሕዝቡ ፡ መግለጥ ፡ ይችላሉ ፡ ምሳሌ ፡ ምስ ፡ ፳፭ ፡ ቍ፪ና ፡ ፯[12] ከብዙ ፡ መቃብያ ፡ ነገር ፡ ተጠንቅቀው ፡ ፳፱ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ቍ ፡ ፳ ፡ ለበጎ ፡ አድራጊውም ፡ እንደ ፡ መጠኑ ? ዋጋውን ፡ ይሰጡታል ፡ ሮሜ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፫ና ፡ ፬ ።[13]

## ስድስተኛ ።

ምንስቴሮች ፡ በልብ ፡ ይመስላሉ ፡ ልብ ፡ የደግና ፡ የክፉ ፡ አሳብ ፡ መብቀያ፡ ነው ፡ እንዲሁ ፡ መልካም ፡ ምንስቴር ፡ መልካም ፡ አሳብና ፡ ምክር ፡ የበቀለ ፡

---

12. ‘‘፪– የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ነገርን ፡ መሠወር ፡ ነው ። የነገሥታት ፡ ክብር ፡ ግን ፡ ነገርን ፡ መመርመር ፡ ነው ። — — — ፮– በንጉሥ ፡ ፊት ፡ ዓይኖችህ ፡ ኢያዩ ፡ ስትዋረድ ፡ ወደዚህ ፡ ከፍ ፡ በል ፡ ብትባል ፡ ይሻልሃልና ።’’

13. አራት ፡ ዘፀአት ፡ ምዕራፍ ፡ ፳፫ ፡ ቍጥር፡፰–‘‘፰፡መማለጃም፡አትውሰድ።መማለጃ፡የብልሃተኞችን ፡ ዓይን ፡ ያሳውራልና ፡ የጻድቃንንም ፡ ነገር ፡ ያጣምማል ።’’ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሰዎች ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፫ ቍጥር ፡ ፫ ፡ እና ፡ ፬ ።
‘‘፫– አለቆቹ ፡ መልካም ፡ በሚያደርግ ፡ ላይ ፡ ለፍርሃት ፡ አይደሉምና ፡ በክፉ ፡ እንጂ ። መኰን ንንስ ፡ እንዳትፈራ ፡ ብትወድ ፡ መልካም ፡ አድርግ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድም ፡ ክብር ፡ ይሆንልሃል ። ፬– የእግዚአብሔር ፡ ሎሌ ፡ ላንት ፡ ነውና ፡ ለበጎ ። ክፉ ፡ ግን ፡ ብታደርግ ፡ ፍራ ፡ በከንቱ ፡ ሰይ ፍ፡አይታጠቅምና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሎሌ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንጂ ። ክፉ ፡ የሚያደርገውን ፡ በቅጣት ፡ በሚበቀል ።’’

እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመንግሥታችንና ፡ ለኀገራችን ፡ ሰላምና ፡ ጤና ፡ ይሆናል ። ከክፉ ፡ ምንስቴር ፡ ክፉ ፡ አሳብና ፡ ምክር ፡ የበቀለ ፡ እንደሆነ ፡ በመንግሥታችንና ፡ በኀገራችን ፡ ጦርና ፡ ረሀብ ። መናቅና ፡ ድንቁርና ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ይመጣል ። ምሳሌ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ፡ ማቴዎስ ፡ ም፲፰ ፡ ቍ ፡ ፲፱ ።[14]

ሰባተኛ ።

ምንስቴሮች ፡ በሆድ ፡ ይመስላሉ ። ሆድ ፡ ለአካል ፡ ሁሉ ፡ ኀይል ፡ ጉልበት ፡ የሚሰጥ ፡ መድኀኒት ፡ ተሸካሚ ፡ ነው ። ለአካል ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ ብርታትና ፡ ደም ፡ ይሰጠዋል ። እንዲሁ ፡ ምንስቴሮችም ፡ ለኀገራችንና፡ ለመንግሥታችን ፡ ጉልበትንና ፡ ኀይል ፡ የሚሆን ፡ የምክር ፡ መድኀኒት ፡ ይሰጣሉ ፡ መዝሙ ፡ ፻፬ ፡ ቍ ፡ ፲፭ ።[15]

ስምንተኛ ።

ምንስቴሮች ፡ በጅ ፡ ይመስላሉ ፡ እጅ ፡ በዕውቀት ፡ ያገኘውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ፡ ሠርቶ ፡ ራሱን ፡ ሐብታም ፡ ያደርጋል ። እንዲሁ ፡ ምንስቴሮችም ፡ በሙሉ ፡ ዕውቀት ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ሥራቸውን ፡ የሠሩ ፡ እንደሆነ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ሐብታም ፡ ያደርጋሉ ፡ ያከብራሉ ፡ ፩ ፡ ተሰሎ ፡ ምዕ ፡ ቍ፲፩ ።[16]

ዘጠነኛ ።

ምንስቴሮች ፡ በግር ፡ ይመስላሉ ። እግር ፡ የአካል ፡ መንበርና ፡ ተሸካሚ ፡ ነው ። አካል ፡ ሁሉ ፡ ያለሱ ፡ መቆም ፡ አይችልም ። እንዲሁ ፡ መንግሥት ፡ ያለ፡ ምንስቴሮች ፡ ምክር ፡ ብቻውን ፡ መቆም ፡ አይችልም ። የመንግሥት ፡ መንበሩና ፡ ዙፋኑ ፡ ጉልበቱም ፡ ምንስቴሮች ፡ ናቸው ። ምሳሌ ፡ ም ፲፭ ፡ ቍ ፡ ፳፪ ።[17]

እነዚህም ፡ አካላት ፡ በስራና ፡ በስም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ አንድ ፡ ሥጋ፡ እንዲባሉ ፡ ምንስቴሮችም ፡ በሥራና ፡ በስም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ ይባላሉ ። ደግሞ ፡ እግር ፡ እኔ ፡ እጅ ፡ አይደለሁም ፡ ብሎ ፡ ከሥጋ ፡ ማኅበር ፡ መለየት ፡ እንዳይችል ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፳፩ ።[18] እንዲሁ ፡ ከምንስቴሮች ፡ አንዱ ፡ የመንግሥት ፡ ማኅበር ፡ የመንግሥት ፡ አገልጋይ ፡ አይደለሁም ፡ ለማለት ፡ አይችልም ።

አካል ፡ ሁሉ ፡ ዓይን ፡ ቢሆን ፡ የመስማት ፡ ሥራ ፡ ወዴት ፡ ይገኝ ፡ ነበረ ። ወይስ ፡ ሁሉም ፡ ጆሮ ፡ ቢሆን ፡ የማሽተት ፡ ሥራ ፡ ወዴት ፡ ይገኝ ፡ ነበረ ፡ ፩ ቆሮ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ።[19] እንዲሁ ፡ ሁሉም ፡ የጦር ፡ ምንስቴር ፡ ቢሆን ። የርሻ ፡ ምንስቴርና ፡ የንግድ ፡ ምንስቴር ፡ ወዴት ፡ በተገኙ ። ሁሉ ፡ የገንዘብ ፡

---

14. "፲፬- መልካም ፡ ምክር ፡ ከሌለ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝብ ፡ ይወድቃል ። በመካሮችም ፡ ብዛት ፡ ደኅንነት፡ ይሆናል ።" ስለ ፡ ማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፰ ፡ ቍጥር ፡ ፲፱ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፰ ተመልከት ።
15. "፲፭- የወይን ፡ ፀጅም ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኝ ፡ ፊቱ ፡ በዘይት ፡ እንዲበራ ፡ እንጀራም ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ እንዲያጸና ።"
16. "፲፩- ከላንትም ፡ ከንዳችሁ ፡ በከንቱ፡እንጀራ ፡ አልበላንም ፡ እንሰራ ፡ ነበር፡እንጅ ፡ በድካምና ፡ በኃዘን ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ከላንት ፡ በማንም ፡ እንዳናከብድ ።"
17. "፳፪- ምክር ፡ ከሌለ ፡ ዘንድ ፡ አሳብ ፡ ይበተናል ፡ መካሮች ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ በሆኑበት ፡ ዘንድ ፡ ትጸናለች ።"
18. ከላይ ፡ ያለውን ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፩ ፡ ይመለከቷል ።
19. ከላይ ፡ ያለውን ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ይመለከቷል ።

ምንስቴር ፡ ቢሆን ፡ የፍርድ ፡ ምንስቴር ፡ ወዴት ፡ ይገኝ ፡ ነበረ ። ራስም ፡ እጆ ችን ፡ እግሮችን ፡ አልሻችሁም ፡ ለማለት ፡ አይችልም ፡ ፩ ቆሮ ፡ ም፲፪ ቍ ፡ ፳፩ ።[20] ሠራተኞች ፡ ናቸውና ። እንዲሁ ፡ መንግሥትም ፡ ሚኒስትሮቹን ፡ አልሻችሁም ፡ ለማለት ፡ አይችልም ፡ ረዳቶቹ ፡ ናቸውና ።

ሁሉንም ፡ በየሥራው ፡ በየሥራው ፡ እግዚአዎሔር ፡ አስቀመጠ ፡ ነገር ግን ፡ አንዱ ፡ ቢታመም ፡ ሁሉም ፡ ይታመማል ፡ አንዱ ፡ ደስ ፡ ቢለው ፡ ሁሉም ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ ፩ ቆሮ ፡ ም ፲፪ ፡ ቍ፳፮ ።[21] እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሠራተኞች ፡ ሥራ ቸው ፡ በስም ፡ ስለ ፡ ተለየ ፡ አገርና ፡ መንግሥት ፡ በመጠበቅ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ ምሳሌ ፡ ምኟ፩ ፡ ቍ ፳፱ ።[22] ያገር ፡ ግዛት ፡ ምንስቴር ፡ በዓይን ፡ ይመሰላል ። የውጭ ፡ ምንስቴርና ፡ የሥልክ ፡ ምንስቴር ፡ በጆሮ ፡ ይመሰላሉ ። የንግድ ፡ ምንስቴር ፡ የርሻና ፡ የሥራ ፡ ምንስቴሮች ፡ በጅ ፡ ይመሰላሉ ። የገንዘብ ፡ ምንስ ቴርና ፡ የርሻ ፡ ምንስቴር ፡ በሆድ ፡ ይመሰላሉ ። የውጪ ፡ ምንስቴር ፡ በልብ ፡ ይመሰላል ። ምንስቴሮች ፡ ባንድነት ፡ የሚሠሩት ፡ የውጪ ፡ መንግሥት ፡ ምስ ጢር ፡ በርሱ ፡ ይፈጸማልና ።

ጳግመኛ ፡ የፍርድ ፡ ምንስቴር ፡ ባፍ ፡ ይመሰላል ። ፈርዶ ፡ ቀጪ ፡ ነውና ። የጦር ፡ ምንስቴር ፡ በግር ፡ ይመሰላል ፡ ኀይልና ፡ ብርታት ፡ ከርሱ ፡ ይገኛልና ። ሁሉም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ናቸው ። ከመንግሥት ፡ ጋራ ፡ ይሠራሉ ።

ዓይን ፡ የማየትን ፡ ሥራ ፡ ትቶ ፡ ጆሮ ፡ ሆኖ ፡ መስማት ፡ እንዳይችል ። እን ዲሁ ፡ አንዱ ፡ ምንስቴር ፡ የቆመበትን ፡ ሥራ ፡ ትቶ ፡ ያንዱን ፡ ሥራ ፡ ለመሥ ራት ፡ ይችል ፡ አይመስልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ በውጭ ፡ የተለየ ፡ ስለ ፡ መሰለ ፡ በምስጢር ፡ ልዩ ፡ አይደለም ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ በንሰለት ፡ የተያያዘ ነው ፡ እንጂ ። የዓይን ፡ ሥራ ፡ ለአካል ፡ ሁሉ ፡ ጥቅም ፡ እንደ ፡ ሆነ ። እንዲሁ ፡ ያንዱ ፡ ምንስቴር ፡ ሥራ ፡ ለምንስቴር ፡ ሁሉ ፡ ጥቅም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ።

ደግሞ ፡ የአካላት ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ አለቃ ፡ የሆነ ፡ ራሳችን ፡ ከሠራተኞቹ፡ ማኅበር ፡ አንዱ ፡ ቢጐድልበት ፡ እንዳይወድ ። እንዲሁ ፡ የምንስቴሮች ፡ ማኅ በር ፡ አለቃ ፡ የሆነ ፡ መንግሥትም ፡ ከሠራተኞቹ ፡ ማኅበር ፡ አንዱ ፡ ቢጐድል ፡ አይወድም ። ነገር ፡ ግን ፡ እያንዳንዱ ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡ ድካሙ ፡ መጠን ፡ ዋጋ ውን ፡ ይወስዳል ። ሁሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ በተሰጣቸው ፡ ሥራ ፡ የማይገባውን ፡ መሥራት ፡ በልቡ ፡ አይመሥረት ፡ አሳቡ ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ።

ከመንግሥት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ (ስለአለን) ከኛም ፡ ዕውቀት ፡ የተ ሠጠችው ፡ እንደውቀቱ ፡ መጠን ፡ አውቀትን ፡ ይናገር ። አገልጋይም ፡ ቢሆን ፡ በማገልገሉ ፡ ይንቃ ። አስተማሪም ፡ ቢሆን ፡ በማስተማሩ ፡ ይትጋ ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፮ና፯[23] ዕውቀትን ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከክፋት ፡ ይድናል ። ነገር ፡ ግን

20. "፳፩- ዓይንም ፡ አይቻላትም ፡ እጅን ፡ ትላት ፡ ዘንድ ፡ አልሻችሁም ። ራስም ፡ ደግሞ ፡ አይች ልም ፡ እግሮችን ፡ ይላቸው ፡ ዘንድ ፡ አልሻችሁም ።"
21. ከላይ ፡ ያለውን ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፩ ፡ ይመለከቷል ።
22. "ብልሃተኛ ፡ የኃያላንን ፡ አገር ፡ ይከፍታል ፡ የሚታመኑባትንም ፡ ኃይል ፡ ያፈርሳል ።"
23. "፮- ነገር ፡ ግን ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ አለችን ፡ በተሰጠችን ፡ ጸጋ ። ከኛም ፡ ትንቢት ፡ የተሰ ጠው ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ መጠን ፡ ትንቢት ፡ ይናገር ። ፯- አገልጋይም ፡ ቢሆን ፡ በማገልገሉ ፡ ይንቃ ። አስተማሪም ፡ ቢሆን ፡ በማስተማሩ ።

እውቀት ፡ እንዴት ፡ ይገኛል ፡ ካልሰሙት ፡ ወይስ ፡ እንዴት ፡ ይሰሙታል ፡ አስተማሪ ፡ ከሌላቸው ። አስተማሪስ ፡ እንዴት ፡ ያስተምራል ፡ መንግሥት ፡ የተማሪ ፡ ቤትን ፡ ካላቆመ ። ሮሜ ፡ ም ፡ ቍ ፡ ፲፬ ።[24] የውቀት ፡ ሁሉ ፡ መሠረት ፡ የውቀት ፡ ሁሉ ፡ መገኛ ፡ የተማሪ ፡ ቤት ፡ ነው ። ለተመለከተና ፡ ለመረመረው ፡ ሰው ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይልቅ ። የተማሪ ፡ ቤት ፡ ይበልጥ ፡ ይመስላል ። የተማሪ ፡ ቤት ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሠረት ፡ እንደሆነ ፡ እንደዚሁ ፡ መንግሥትም ፡ ለተማሪ ፡ ቤት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ለማደላደልና ፡ ለማስማማት ፡ የተመረጣችሁ ፡ ክቡራን ፡ ምንስቴሮች ፡ ሆይ ። አስቀድማችሁ ፡ የተማሪ ፡ ቤትን ፡ ለማቆም ፡ ቻል ፡ አትበሉ። የብልሐትና ፡ የውቀት ፡ ምንጭ ፡ የተማሪ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቃችኋልና ። እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ባጼ ፡ ሚኒልክ ፡ ዕውቀት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተጠብቃ ፡ ትኖር ፡ እንደነበረች ። እናንተም ፡ እንዲሁ ፡ የልባችሁን ፡ ዕውቀትና ፡ አሳብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መዘርጋት ፡ ያስፈልጋችኋል ።

እኔም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ወገን ፡ የምሆን ። በድንቁርና ፡ ዘመኔን ፡ ያሳለፍኩ ። ዕውቀት ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ የራቀኝ ፡ እንደ ፡ መጠኔ ፡ መንግሥትን ፡ በራስ ። ምንስቴሮችንም ፡ ባካላት ፡ መስዬ ፡ ስላሳሰብኋችሁ ። ድፍረት ፡ እንዳይሆንብኝ ፡ እለምናለሁ ። ትልቅ ፡ ሆነ ፡ ትንሽ ፡ ሆነ ፡ ላገሩና ፡ ለመንግሥቱ ፡ የማይቀና ፡ የለም ።

የኢትዮጵያ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መኃተሚያ ።

24. "፲፬- ነገር ፡ ግን ፡ እንዴት ፡ ይጠሩታል ፡ የማያምኑበት ። ወይስ ፡ እንዴት ፡ ያምናሉ ፡ ያልሰሙት ወይስ ፡ እንዴት ፡ ይሰማሉ ፡ አስተማሪ ፡ የሌላቸው ።"